# ኛሮስኸሁኔጎ



አገልጋይ ዮናስ ዘርጳ

መስከረም/2011

## ምስጋና

ለስሙ ክብርና ለቤተ-ክርስቲያን ጥቅም የታናናሾችን እጅ ለመልካም ሥራ የሚያነሳሳ አስጀምሮም የሚያስፈጽም ልዑል እግዚአብሔር ስለዚህ ሥራ ክብር ምስጋና ይግባው፡፡ የጽሁፉን ሥራ በማረምና የበሰሉ አስተያየቶችን በመስጠት በቅንነት ለረዳኝ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን የወጣቶች ዋና ፀሐፊ ወ/ዊ በሰላሙ በካሎ የላቀ ልባዊ ምስጋናን ማቅረብ እወዳለሁ፡፡
ለዚህ ሥራ መሳካት ቀኝ እጃቸውን ለሰጡኝ ለውድ ወንድሜ አብርሃም ዘርጻ፣ በፀሎት ላገዘችኝ ለውድ እናቴ ሽግኝ ከፌና እንዲሁም የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ባጠቃላይ በሚታይ በማይታይ ነገር ሁሉ ላገዙኝ ወገኖች ጌታ የልባችሁን ያድርስ እሺ ይበላችሁ ማለትን እወዳለሁ፡፡ የኮምፒውተር ጽሁፉን በመተየብ እና የዲዛይን ከቨሩን በመስራት አጋር ለሆንከኝ ውድ ጓደኛዬ ታሪኩ ሐርኪሶ እግዚአብሔር ፀጋውን ያብዛልህ፡፡

## ስጦታ

ይህ መጽሐፍ በሕይወትህ እንዲያገኙህ ወደምትፈልጋቸው በረከቶችህ ትገባ ዘንድ አስፈላጊ የሆነውን የአምልኮ ቁልፍ በእጅህ እንድታስገባ ከእግዚአብሔር የሆነ ስጦታ ነው፡፡አንተ ደግሞ የምትወደውን ለምትወደውና አምልኮ (ፕሮስኩኔኦ) ያስፈልገዋል ብለህ ለምታስብለት ወዳጅህ በስጦታ አበርክት፡፡

*ሺህ አመት በፊቱ እንደ አንድ ቀን ሳለች*

*ለእርሱ ጊዜ አጥቼ የእኔው ቀን አጠረች*

*ከጊዜዬ እራፊ ለአምላኬ ብሰጠው*

*መሀሌን ክብር ሆኖ ዙሪያዬን አጠረው፡፡*

*በእድሜዬ የሠራሁት ትልቁ ኃጢአት*

*ለዘመናት ጌታ ጊዜ አጣሁ ማለት*

*ዘመኔ እንዲሆን የዕረፍት የበረከት እኮ*

*በክብሩ ውስጥ ዘመርኩ ተገኘሁ በአምልኮ*

ለ ________________________________________

ከ ________________________________________

ቀን ____________________

ፊርማ____________________

# ማውጫ

መግቢያ ......iii

መቅድም ......v

ምዕራፍ አንድ ......1

1.1 የአምልኮ ምንነት፡- ......1

1.2. እውን አምልኮ ......7

1.3. አምልኮ ለንጉሱ የሚቀርብ ነው። ......7

1.4. አምልኮ ዋጋ በመክፈል የሚፈጸም ጉዳይ ነው። ......8

1.5. አምልኮ ከስግደት ጋር የተያያዘ ነው። ......8

1.6. አምልኮ ስጦታን ማቅረብንም ይጨምራል ......8

ምዕራፍ ሁለት ......14

2.1. አምልኮ ከሙሴ በፊት ......14

2.2. ሙሴና የማደሪያ ድንኳን ......17

2.3. የምኩራብ አምልኮ፡- ......18

2.4. ሙዚቃ በቤተመቅደስ ......19

2.5. ጌታ ኢየሱስና አምልኮ ......20

2.6. የጥንቷ ቤተ-ክርስቲያን፡- ......22

2.7. አምልኮ በጳውሎስ ዘመን፡- ......22

ምዕራፍ ሦስት ......24

3.1. የአምልኮ እቅድ አውጪ እንደ ካህንና ነብይ፡- ......32

3.2. የአምልኮ ዕቅድ አውጪነት መልካም ባህሪያት፡- ....................................33
3.3. የአምልኮ ጊዜ ቃሎቻችን....................................37
3.4. የአምልኮ ሥርዓት፡- ከክርስቲያናአዊ ልምምድ ጥበብን መማር....................................42
ምዕራፍ አራት....................................45
4.1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዳሰሳ፡-....................................45
ሀ) በብሉይ ኪዳን....................................45
ለ) በአዲስ ኪዳን፡-....................................49
4.2. በአዲስ ኪዳን የአምልኮ መገለጫዎች....................................51
4.2. የአዲስ ኪዳን አምልኮ መገለጫዎችን ሰብሰብ አድርገን እንደሚከተለው ....................................52
ምዕራፍ አምስት ....................................55
5.1. ልዩ ልዩ አምልኮ፡- ....................................55
5.2. ስፍራ የማይገታው አምልኮ፡-....................................56
5.3. በመንፈስና በእውነት ማምለክ፡- ዮሐ 4 ....................................57
ዋቢ መጽሐፍ / Bibliography/....................................69

# መግቢያ

የክርስቶስ ሰላምና ፀጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን!! ውድ የፕሮስኩኔኦ አንባቢዎች እንደምን ከረማችሁ፡፡ በተለያዩ ሁኔታዎች ዘግይተን ብቅ ብለናል፡፡ በፀሎታችሁ ለምታስቡን በማንበብና ያላችሁን በማካፈል፤ በሃሳብም ለምትተባበሩን ሁሉ የጌታ በረከት ለእናንተ ይሁን!!

የእግዚአብሔር ቃል *"ሳታቋርጡ ፀልዩ"* ይላል፡፡ በተለይም ሐዋሪያው ጳውሎስ በኤፌሶን 6፡18 ላይ እንሚያሳስበው ውጊያው መንፈሳዊ ነውና በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ በመታመን በፀሎት እንድንጋደል ያስፈልጋል፡፡ ስለቅዱሳን በተለይም ስለሚያገለግሉን የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ልንማልድ ይገባል፡፡ ለቤተ-ክርስቲያን መሪዎች፤ ለሙሉ ጊዜ አገልጋዮች፣ ለወንጌል ሰባኪዎች፣ የሃገር መሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ ተማሪዎች እግዚአብሔር ራሱ እንዲያነቃቃቸው፤ እየቀደሳቸውና እያነፃቸው ለሚያገለግሉትም ሕዝብ በረከት እንዲያደርጋቸው ጊዜ ወስደን መፀለይ ይገባናል፡፡

በቤተክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች መካከል እውነተኛ የመንፈስ አንድነት እንዲኖር፤ ራዕይ እንዲሰጣቸውና ራዕያቸውንም በሥራ እንደተረገሙ ጉልበትና ብርታትም እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ የኔም ፀሎት ነው፡፡

የአምልኮ ምንነት የሚገባን ስናመልክ ብቻ ነው፡፡ ከምንተረጉመውና ከምንረዳው በላይ የአምልኮ ሕይወታችን ባደገ ቁጥር ከፍ ወዳለ የአምልኮ ትርጉምና ኃይል እንደርሳለን፡፡ የዚህ መጽሐፍ ዋነኛ ዓላማም ስለአምልኮ ያለንን የተዛባ አመለካከት እንደ እግዚአብሔር ቃል መስመር በማስያዝ ወደ ጣዕመ አምልኮ እንደርስ ዘንድ በቃል ውስጥ የተገለፀውን አስደናቂ የአምልኮ ህይወት ማሳየት ነው፡፡

ይህ ትውልድ ከገባበት የተወሳሰቡ ችግሮች ይልቅ በጣም አስፈሪ ችግሩ አለማምለኩ ነው፡፡ በር ሊዘጋ ይችላል የመክፈቻው ቁልፍ መጥፋቱ ግን የበለጠ ያስፈራል፡፡ በሌላ አነጋገር አምልኮ የማንኛውም ዓይነት ግላዊ፣ ቤተሰባዊ፣ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ችግሮች መፍትሔ ማግኛ ቁልፍ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ መጽሀፍ ይህን እውነት በጥልቀት የምንረዳበትና የአምልኮ ህይወታችንን ለመለወጥ ተግባራዊ ልምምድ የምንጀምርበት መጽሐፍ ነው፡፡ በመጽሀፉ ውስጥ

- ✓ ስለ አምልኮ ሊኖርህ የሚገባውን መንፈሳዊ ግንዛቤ
- ✓ ከአምልኮ በፊት ልታደርግ ስለሚገባው የአምልኮ ዝግጅት
- ✓ በአምልኮ ሰዓት እንዴት ማምለክ እንዳለብህና
- ✓ ከአምልኮህ በኋላ ስለምታገኘው መንፈሳዊ ኃይልና ፀጋ በሰፊው ታገኛለህ፡፡

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለፁትን ልምምዶች በብዙዎች ሕይወት በተግባር ተሞክሮ አስደናቂ ለውጥ አምጥቷል፡፡ ሰባት ጊዜ በእሳት ከተፈተነ ወርቅ በላይ እጅግ የነፃው የአምላክ ቃል ዛሬም ብዙዎችን ነፃ ያወጣል፡፡ አሁን ተራው የአንተ ነው፡፡ የአምልኮ ሕይወትህን አስተካክልና ሰላምና በረከትን ገንዘብህ አድርግ፡፡

አዘጋጁ!

# መቅድም

የምድርን ገፅ እና የሰው ልጆችን ታሪክ ያበላሸው የመጀመሪያው ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር ህብረት ለይቶታል ይህም ታላቁ ሞት ነበር። በደም ዋጋ ያ ህብረት ከታደሰ በኋላ ሰው እግዚአብሔርን እንደ አባት ፊት ለፊት ማየት ችሏል።

ዛሬ በመላው ዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖች የክርስትና አመጣጥ፣ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ጊዜና ምክንያት፤ ከዚያም አለፍ ብሎ ሰው የነበረበትን ሁኔታ ከመጀመሪያው ሰው አዳም መጀመሪያና መጨረሻ ድረስ ከመጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው የምንረዳው ስለ አምልኮ ነው።

እግዚአብሔርም እኛን የፈጠረው ለዚህ ዓላማ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ የተሻለ መጽሐፍ የለም፤ አይኖርምም። መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ ስለ ሰው ሕይወት፣ የዘላለም ደህንነትና፣ ክርስትናን ስለማስፋፋት ሀሳብ የሚሰነዝር መጽሐፍም ለዘመናችን እጅግ አስፈላጊ ነው። የአምልኮ ሕይወታችን ሲስተካከል መላው ህይወታችን ይለወጣል። አምልኮ የማይለወጠውን ለዋጭ ማግኘት ነውና።

- የአምልኮ ሕይወትህ እንዲስተካከል ትፈልጋለህ?

ከፈለግህ በርግጥ ይለወጣል። ነገር ግን ፍላጎት አንዱ እንጂ ብቸኛው መፍትሔ ባለመሆኑ ወደ ተግባር ልምምድ መግባት ያስፈልገሃል።

አንባቢ ሆይ አስቀድሜ እንዳልኩት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለፁት መንፈሳዊ ልምምዶች ብዙዎችን ወደ ተለወጠ የአምልኮ ህይወትና እረፍት አሻግረዋል። አሁን የማረጋግጥልህ በመጽሐፉ ውስጥ የተገለጹትን የአምልኮ እውነታዎች በትጋት ብተገብር የአምልኮ ህይወትህ እና አጠቃላይ የህይወትህ

አቅጣጫ መዋቅሩ ታድሶ በላቀ ማንነት እንደምትቆም ላረጋግጥልህ እወዳለሁ፡፡

የአምልኮ ህይወቴ እንዲስተካከል እፈልጋለሁ ብለህ የለ? እንግዲያስ ይህን መጽሐፍ አንብበህ አታስቀምጠው፤ ይልቁንም በጥሞና ማስተዋል ጀምር፤ እውነታውን መረዳቱ ማምለክን ቀላል ያደርገዋልና፡፡

ስለዚህ በመጽሐፉ ውስጥ ከእያንዳንዱ ርዕስ ቀጥሎ ለአምልኮ ህይወትህ መለወጥ ወሳኝ የሆኑ ተግባራትን ለመጀመር ቃል እንድትገባ ትጠየቃለህ፡፡ ፈቃደኝነትህንና ጥቂት ጥረትህን የሚጠይቁ ተግባራት ናቸው፡፡ አንባቢ ሆይ ቃል እንድትገባልኝ የምሻው እውነታዎቹን እንድትወዳቸው፤ እንድትመሰጥባቸው፣ የአንተ እንድታደርጋቸውና በአምልኮ ውስጥ በትጋ እንድትገለገልባቸው ነው፡፡ ይህን ማድረግ ከባድ ነውን? አሁን ካለህበት ህይወት ይልቅ የሚከብድ አይመስለኝም፡፡ ቀላል ህይወት ለመኖር ግን ቢከብድህም አድርገው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

*“ስለ አምልኮ ያለህን ግንዛቤ አስፋና አምልኮህን ቀላል፣*

*ግልጽ፣ እጅግ አስፈላጊና አስደሳች አድርገው፡፡”*

## 1.1 የአምልኮ ምንነት፡-

በጥንቱ አንግሎ-ሳክሰን የእንግሊዘኛ ቋንቋ “አምልኮ” (worship) የሁለት ቃላት ቅንጅት (Woerth and scipe ) ሲሆን መንፈሳዊ ፍቺውም ለማንነቱ የሚገባውን ክብር መስጠት ማለት ነው፡፡ ቃሉ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይኖርም አምልኮ በእብራይስጥ ሻካ፣ በግሪኩ ፕሮስኩኔኦ ሲባል ትርጓሜውም ለበላይ ባለስልጣን ለጥ ብሎ እጅ በመንሳት የሚገባውን ክብር መስጠት ማለት ነው፡፡

አምልኮ፡- ኃይልና ባለጠግነት፣ጥበብና ብርታት፣ክብርና ሞገስ ሊቀበል የሚገባውን እግዚአብሔርን በትሁት መንፈስ እንደ ፈቃዱ እያገለገሉ በታላቅነቱ የሚገባውን መልስ መስጠት ነው፡፡ (1ዜና 16፡28-29) እንዲህ ይላል "*ክብርንና ኃይልን ለእግዚአብሔር አምጡ፤ ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር አምጡ፡፡ ቁርባንን ይዛችሁ በፊቱ ግቡ፣በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ፡፡*" ይላል፡፡ በተጨማሪም (መዝ 29፡1-2፣ ራዕ 4፡10-11፤ ራዕ 5፡11-14) ይህንኑ ያጠንክርልናል፡፡

ሆኖም የመዝገበ ቃላት ትርጉም ብቻ አምልኮን በወጉ አይገልጸውም፡፡አመርቂ ትርጉም የሚኖረው በአውደ ምንባቡ መሠረት

የተረጎምን እንደሆነ ነው፡፡ እዚህ ላይ አንድ አጭር ታሪክ ልንገራችሁ፡-

*በለጠችና ባሏ አምልኮተ ባዕድን ትተው ክርስቲያን ሆነዋል፡፡ ክርስቶስ በሰጣቸው አዲስ ህይወት ደስ ብሏቸዋል፡፡ አንድ ቀን ባልየዋ ከእናቱ ጋር ወደ ቀብር ሄደ እናቱ ገና ጣዖትን የሚያመልኩ ነበርና እሱም ከርሳቸው ጋር እንደቀድሞው የሰይጣንን ሥራዓተ-አምልኮ ተካፈለ፡፡ ይህም አድራጎቱ ከጌታው ጋር የነበረውን አንድነት አቋረጠበት፡፡ አንድነታቸው እንደቀድሞ አልነበረምና በለጠችም ባልዋ ወደ ቀድሞ አምለኮ እንደተመለሰ አወቀች፡፡ ባሏ ከዚያ ቀን ጀምሮ ወደ ቀድሞው የሰይጣን አምልኮ እንድትመለስለት በለጠችን በየጊዜው ይገፋፋት ነበር፡፡ እርሷ ግን ሰይጣንን ማምለክ እምቢ አለች፡፡ ሰይጣንን ከማምለክ በቀር ግን የሚያዛትን ሁሉ ለመፈጸም ፈቃደኝነትዋን ገለጸችለት፡፡ እርሱም ይህን ምክንያት አድርጎ የሆነ ያልሆነውን አድርጊ በማለት አስቸገራት፡፡*

*አንድ ቀን ሌላ ሚስት ይዞ መጣ፡፡ ይህን ያደረገው መቼም በለጠችን በይበልጥ ለማስጨነቅ ነበር፡፡ ዳሩ ግን በሁለቱ ሴቶች መካከል እውነተኛ ፍቅር ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተፈጠረ፡፡ እንዲያውም ፍቅራቸው እየጋለ ሄደ እንዴት ብትሉ በለጠች ሴትየዋን ወደ ክርስቶስ ስለመራቻት ነው፡፡ ቀስ በቀስ የባልዋም ልብ መለወጥ ጀመረ፡፡ ለሱ ሲበዛ ትዕግስተኛ ነበረችና አንድ ቀን እንዲህ አላት፡፡ "በፍቅርሽና በትዕግስትሽ ተማረኩ!" ብሎ አላት፡፡ ወዲያውም ንስሐ ገባና ወደ ጌታ ተመለሰ ፡፡*

በቤታችሁ እንዲህ ያለ ችግር ቢያጋጥማችሁ እግዚአብሔር ሊረዳችሁ እንደሚችል ታምናላችሁ? በሙሉ ልብ እግዚአብሔርን የምታመልኩ ሁኑ፤ እግዚአብሔር ነገሮቻችሁን በስውር ይሰራል፡፡

✧ ሌላው የአምልኮ ትርጉም፡-

*“ዕዝራም በሕዝቡ ሁሉ ላይ ከፍ ብሎ ሕዝቡ ሁሉ እያዩ መጽሐፉን ገለጠ በገለጠው ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ቆሙ። ዕዝራም ታላቁን አምላክ እግዚአብሔርን ባረከ። ሕዝቡም ሁሉ እጃቸውን እየዘረጉ አሜን! አሜን! ብለው መለሱ፤ ራሳቸውንም አዘንበሉ በግንባራቸውም ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ።”* ነህ 8፡5-6

- አምልኮ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ “አቦድ” /Abad/ ተብሎ ሲጠራ በግሪክ ደግሞ “ላትርያ” / Latreia/ ተብሎ ይጠራል። ይህም ለአንድ ጌታ ብቻ የተገዛ ባሪያ ሊያቀርበው የሚገባ ፍፁምና ሁለንተናዊ አገልግሎት ማለት ነው።

ስለዚህ አምልኮ በክርስቶስ ደም የተዋጀ፣ የተቀደሰና ለእርሱ የተለየ ሕዝብ እግዚአብሔርን በማወቅ በግልና በህብረት ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ብቻ በፍጹም መስጠት፣ መታዘዝ፣ ፍቅርና ትህትና ዘወትር በመንፈስና በእውነት የሚያቀርበው ምስጋና፣ ዝማሬ … ወ.ዘ.ተ ማለት ነው። የተቀደሰ መስዋዕት ሲሆን ደግሞ ካለን ነገር ሁሉ ለወንጌል አግልግሎት መስጠትና መልካሙን ሥራ ሁሉ መፈፀምን እንዲሁም በተሰጠና በተቀደሰ ሕይወት ለእግዚአብሔር ክብር መኖርን ያጠቃልላል። በሌላ አባባል የሰው በሁለንተናዊ ህይወቱና ኑሮው ላይ እግዚአብሔርን ማንገስ ማለት ነው። መዝ 2፡6, 5፡7, 138፡2, ሕዝ 20፡10) በተጨማሪም አምልኮ፡-

- ✓ ለእግዚአብሔር የምስጋና መስዋዕት/ የከንፈሮችን ፍሬ ማቅረብ ነው። (ዕብ13፡15-16)
- ✓ ለምህረቱና ለቸርነቱ ምላሽ መስጠት ነው። (መዝ 100፡1-5)

- ✓ ለብቻው እውቅናን መስጠት፡፡ ( ነህ 9፡6)
- ✓ በፊቱ ራስን መዋረድ ነው፡፡ (መዝ 95፡6-7)
- ✓ በመንገዱ እግዚአብሔርን መምሰል ነው፡፤ (መዝ 96፡9)
- ✓ ራስን ለእግዚአብሔር ማቅረብ (ሮሜ 11፡ 35, 12፡1) ሲሆን ድርጊቱም በእውነትና በመንፈስ ሊሆን ያስፈልጋል፡፡

<u>አምልኮ የሚገባው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው</u>

<u>*ምክንያቱም ፡-*</u>

- ✓ እግዚአብሔር ለስሙ የሚቀና ቀናተኛ ክብሩን ለማንም የማይሰጥ ኃያል አምላክ ስለሆነ ነው፡፡ (ዘፀ 20፡4-6, ዘዳ 6፡13-15, ኢሣ 42፡8)
- ✓ እግዚአብሔር የአማልክት ሁሉ አምላክ፣ የነገስታት ሁሉ ንጉስ የጌቶች ሁሉ ጌታና ሁሉን የሚገዛ አምላክ ስለሆነ ነው፡፡ (መዝ 24፡10, ኢሳ 6፡ 1-4, ራዕ 4፡8)
- ✓ እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪና አምላክ ስለሆነ ነው፡፡ (መዝ 95፡1-5, ራዕ 4፡10-15)
- ✓ እግዚአብሔር አምላክ የሰውን ልጅ የፈጠረበት, እንደገናም ለራሱ የሚሆን ልዩ ሕዝብ ያዘጋጀበት ዋና ዓላማው እርሱን ብቻ እንዲያመልኩት ነው፡፡ (ዘዳ 7፡6, ቲቶ 1፡14, ዕብ 9፡13-14)
- ✓ እግዚአብሔር በጠላቶቻችን ላይ ታላቅ ድል የሚሰጠን እርሱን ብቻ ስናመልክ ነው፡፡ (2ዜና 20፡20-22, መዝ 149፡6)

- ✓ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር፣ መታዘዝ፣ አክብሮትና በእርሱ መታመን የምንገልጽበት መንገድ እርሱን ብቻ በማምለክ ነው፡፡ (ዘዳ 13፡4, ኢ.ያ 22፡9)

<u>**አምልኮና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች**</u>

- ❖ እግዚአብሔርን በማወቅ ማምለክ፡- እግዚአብሔር ፍቅር፣ ቅዱስ፣ ጻድቅ፣ ኃያል አምላክ ፈጣሪያችን ብቻ ሳይሆን ዛሬም ለዘላለምም አባታችንና የነፍሳችን ተስፋ መሆኑን በማወቅ ማምለክ ይጠበቅብናል፡፡ (መዝ 46፡10, ኤር 9፡24 ሐዋ 17፡17-25)
- ❖ እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል፡፡ (ዮሐ 4፡23-24, ራእ 1፡10)
- ❖ ሁለንተናን ህያውና ቅዱስ መስዋዕት አድርገን ለእግዚአብሔር በመስጠት ልናመልከው ይገባል፡፡ ከመስዋዕት ሁሉ ይልቅ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው በተሰጠና በተቀደሰ ሕይወት በትህትና በፊቱ መቅረብ ነውና፡፡ ት.ሚክ. 6፡6-8፣ ሮሜ 12፡ 1-2)
- ❖ እግዚአብሔርን ማምለክ ታላቅ ሥራ መሆኑን በማወቅ ማምለክ አለበን፡፡ ( 2ዜና 25፡ 30-3፣ ት.ዮናስ 3፡8-9)
- ❖ በመዝሙር በውዳሴና በመንፈሳዊ ቅኔ ለእግዚአብሔር የሚገባውን የምስጋና መስዋዕት በማቅረብ (ኤፌ 5፡ 19, ቆላ 3፡16-17, መዝ 98፡9, 50፡23)
- ❖ እግዚአብሔርን በመስማት ፣ በመታዘዝ፣ ጌታ ከሰጠን ነገር ሁሉ በመስጠትና በማካፈል ማምለክ (ያዕ 1፡2፣ ሉቃ 21፡14)
- ❖ በክርስቶስ ደም እንደታጠብን ሁሉ ለእርሱ በመለየት በቅድስናና በንጹህ ህሊና ልናመልከው ይገባናል፡፡ (ዘፍ 35፡2-3- ዕብ 9፡14- 2ጢሞ 2፡3)

- ❖ እግዚአብሔርን በመውደድ ከልብና ከነፍስ ፈቃድ በመሰጠት ህይወት ማምለክ። (ዘዳ 6፡4-5, 1ዜና 28፡9, ኢያ 24፡15)
- ❖ በፈርሃ እግዚአብሔር እግዚአብሔርን ማምለክ። (መዝ 5፡7, ሐዋ 10፡23)

✪ <u>የአምልኮ እንቅፋቶች</u>

- ❖ በኃጢአት ልምምድ ውስጥ መኖር (ምሳ 5፡22)
- ❖ የይቅርታ ልብ ማጣት (ማቴ 5፡23-26)
- ❖ የመንፈስን አንድነት ማጣት (ኤፌ 4፡3፣ ፊል 2፡1-2)
- ❖ አምልኮን በመቃወም የሚደረግ መናፍስታዊ አሠራሮች
- ❖ ልማዳዊ የሆነ ሕግና ስርዓት መፈፀም (2ጢሞ 2፡5)
- ❖ ለአምልኮ የሚገባ ጊዜ አለመስጠት (ሉቃ 10፡ 40-42)
- ❖ የህይወት አለመሰጠትና ለአምልኮ በቂ ዝግጅት አለማድረግ (መንፈሳዊና ቁሳዊ ዝግጅት)

✪ እግዚአብሔርን የማምለክ በረከቶች (ዘፀ 23፡25-31)

እግዚአብሔርን እንደ ቃሉ ማምለክና ለእርሱ የሚገባውን ክብር መስጠት በቤተ-ክርስቲያንም ሆነ በአማኞች ሁለንተናዊ ህይወት ትልቅ ፈዉስና በረከት እንደሚያመጣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተለውን ማስረጃ ይሰጠናል።

- ❖ የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት (ሐዋ 11፡1, መዝ 29፡7-9, ራዕ 1፡10)
- ❖ ሰማያዊና ምድራዊ በረከት መንፈሳዊና ስጋዊ  ፈውስ ማግኘት (ዘዳ 11፡13-15, ዘፀ 20፡24)
- ❖ ረጅም እድሜ መጥገብ (ዘፀ 23፡26)
- ❖ የእግዚአብሔርን ክብር ማየት ። ( 2ዜና 7፡1, 1ነገ 8፡10-11)

❖ የጠላትን ሥራና ሐሳብ መፍረስ። (2ዜና 20፡21-25, ሐዋ 16፡25-26)

❖ ከማንኛውም ተጽዕኖ ነፃ መውጣት (2ቆሮ 3፡16)

❖ የእግዚአብሔርን መከበርና ደስ መሰኘት። (ራዕ 5፡11-14, 4፡8-15, ዕብ 11፡28)

❖ በክርስቶስ ሰላምና በመንፈስ ቅዱስ ደስታ መሞላት (መዝ 95፡1-2, ፊል 4፡7, ሮሜ 14:17)

❖ የእግዚአብሔር መገኘት ወይም አብርሆት ። (ማቴ 20፣ 18፡ ራዕ3፡20, 2ዜና 7፡1-3)

## 1.2. እውን አምልኮ

✧ ሁሉ ነገር ከእርሱ፣ በእርሱና ለእርሱ ስለሆነ አምልኮ እውን የሚሆነውም፡-

1) እግዚአብሔር በፀጋው ለኛ ያለውን መልካሙን ዓላማ፣ ዕቅዱንና ፈቃዱን ሲገልጽልን ነው።

2) ከእርሱ ጋር በክርስቶስ በኩል የተገኘና በመንፈስ ቅዱስ የተገለጸ መልካም የግል ሕብረት ሲኖረን ነው።

3) በደስታ የተሞላ የማክበር፣ የማንገስ፣ በትህትና ራስን የማስገዛትና የመታዘዝ ህይወት ሲኖረን ነው።

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 2፡1-13 ስናነብ አምልኮ በአራት መልኩ ተገልጾ እናያለን።

## 1.3. አምልኮ ለንጉሱ የሚቀርብ ነው።

✧ አምልኮ ንጉሡ ኢየሱስ ሕፃን ቢሆንም እንኳ ለርሱ የሚቀርብ ነገር ነው። ሰባ ሰገል እንደመጡ ሲናገሩ ሄሮድስ በዓላማቸው አግባብነት ጥያቄ

ኖሮት ሳይሆን ነገር ግን ይህ ስግደትን ሊቀበል ያለው ሕፃን ነገ የሱ ዙፋን ተቀናቃኝ እንደሚሆን በመገመት ብቻ በተንኮልና በቅናት ክፉ ሀሳብ አሰበ፡፡ (ማቴ 2፡5, 12-13)

## 1.4. አምልኮ ዋጋ በመክፈል የሚፈጸም ጉዳይ ነው፡፡

እነዚህ ጠቢባን ከሩቅ ስፍራ ተጉዘው መጥተው ለንጉሱ የሚቀርብ ስግደት እንደፈጸሙ እንመለከታለን፡፡ እንዲሁም በ2ኛሣሙ 24፡18-25 ስንመለከት ዳዊት ለእግዚአብሔር መስዋዕትን ያለዋጋ ማቅረብ እንዳልፈለገ እንመለከታለን፡፡ በሕብረት ጉባኤ እግዚአብሔርን ከቅዱሳን ጋር ለማምለክ ዋጋ መክፈል ያህል ሊሰሙን የሚችሉ እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለብን የሚያመለክተን እንደሆነም እንመለከታለን፡፡

## 1.5. አምልኮ ከስግደት ጋር የተያያዘ ነው፡፡

በዚህ ስፍራም ሆነ በተለያዩ ስፍራዎች መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስንመለከት አምልኮ ወድቆ ከመስገድ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ማለትም አምልኳችን ለእግዚአብሔር ስለ እርሱነቱ/ስለማንነቱ/ ስላደረገልን በጎና ታላቅ ነገር በስግደት ሊገለጽ ይቻላል፡፡ (ዘፍ 24፡26-27፡52, ዘፀ 4፡31, ዘፀ 34፡8, መሣ 7፡5) ይህም ስግደት ከምስጋና ዝማሬ ጋር ተጣምሮ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ሊሆን ይችላል፡፡ 2ዜና 7፡3-4, 29፡19-30, ነህ 8፡6)

## 1.6. አምልኮ ስጦታን ማቅረብንም ይጨምራል

የእነዚህ ሰባ ሰገል አምልኮ ስጦታን ማቅረብንም የጨመረ ነበር፡፡ ከስግደታቸው ጋር በተጨማሪ ስጦታን ሰጡት፡፡ ስጦታ ስንል ዝም ብሎ መናኛ ስጦታ ሳይሆን የከበረና ውድ የሆኑ ስጦታዎችን ነበር አምጥተው

ይሰጡት፡፡ ከዚህ ጋር በተመሳሰለ ስጦታንና መባን በመስጠት እግዚአብሔር እንደሚመለክ ቃሉ ይነግረናል፡፡ (ዘፀ 25፡1-2, 35፡5-ዘኁ 31፡50, 2ኛ ሳሙ 8፡11, 1ኛ ዜና 29፡ 6-9, ዕዝ 8፡28, ምሳ 3፡9)

አምልኮን በተመለከተ ልናውቀው የሚገባን እውነት ሰይጣን እንኳ በብርቱ የሚፈልገውና የሚጠማው ነገር መሆኑን ነው፡፡ ሰይጣንም ብቻውን አምልኮን ይፈልጋል ለሚያቀርብለትም ወሮታ ለመክፈል ዝግጁ ነው፡፡ ጌታም አምልኮን ይሻል፡፡ አምላክ እንደሆነና መመለክ ያለበት እርሱ ብቻ መሆኑን ነግሮናል፡፡ በቃሉም አጽንቶናል፡፡ ይህም አምልኮ ለእግዚአብሔር እንጂ ለማንም እንድንሰጥ የማያስፈልግ መሆኑን ያስገነዘብናል፡፡ አምልኮ ከስግደት ጋር መያያዙን ከላይ ካየነው ጥቅስ እንረዳለን፡፡ሰይጣንም ስገድልኝ ያለው ለዚህ ነው፡፡ ጌታም ሂድ አንተ ሰይጣን ጌታ አምላክህን ብቻ አምልክ ለእርሱም ብቻ ስገድ ተብሎ ተጽፈዋል ብሎ ገሰፀው፡፡

ኢየሱስ ምንም የድርድር መድረክ አልከፈተም የዓለምን ሕዝብ ከሰጠኸኝ እስግዳለሁ ነገር ግን አላመልክህም አላለም፡፡ ይህም አምልኮና ስግደት ሁለቱ የማይነጣጠሉ የተያያዙ ነገሮች እንደሆኑ ያረጋግጥልናል፡፡አምልኮ የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ እስኪ ለጥቂት ጊዜ ቆም ብለን እናስብ ሰይጣን ስለአምልኮ ሲል የዓለምን መንግስታትና ክብራቸውን ሁሉ ለመስጠት ፈቃደኛ ነው፡፡ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች በእውነት እነዚህን መንግስታት ለመስጠት ቀድሞውኑ የእርሱ ናቸው ወይ? ብለው ይጠይቃሉ ለመልሱም መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ቦታ ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዥ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ዮሐ 12፡31, 14፡30, 16፡11, 2ቆሮ 4፡4)

በአጠቃላይ ግንዛቤ መጽሐፍ ቅዱስ ከአዳምና ከሄዋን ውድቀት በኋላ ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዥ እንደሆነ ያሳየናል፡፡ ሰይጣን ጌታን በምድረ በዳ ሲፈትነው በቀላል አልነበረም፡፡ ፈተናው ብዙ ሊታሰቡ የሚችሉ ሀሳቦች ያዘለ ነበር፡፡ አንደኛው ሀሳብ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣበት ዋነኛ ዓላማ "ዓለምን ለማዳን" ነው፡፡ ሰይጣን ደግሞ ጌታ ወድቆ ከሰገደለት ዓለምንና በዓለም ያለውን በአቋራጭ ሊሰጠው እንዳሰበና የክርስቶስ የመስቀል መከራ አስፈላጊ ያልሆነና ይህ ሁሉ ስቃይ ሊደርስበት እንደማይገባ ለክርስቶስ እየነገረው መሆኑ ነው፡፡

ዲያብሎስ ሞኝ አልነበረም እግዚአብሔር ምነኛ ዓለምን ወዶ አንድ ልጁን እንደላከ ያውቃል፡፡ ስለሆነም ይህን አጭርና ፈታኝ መንገድ አቀረበለት " *ወድቀህ ብትሰግድልኝ...*" እግዚአብሔር ዓለምን መውደዱ እውነት ቢሆንም አምልኮና ስግደት የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ይህን የሚያስለውጥና የሚያስቀር አንዳች ነገር ሊኖር አለመቻሉን ክርስቶስ ከሰጠው መልስ በግልጽ እንረዳለን፡፡ በእርግጥም አምልኮና ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

የእስራኤል አምልክ እውነተኛ አምላክ ስለሆነ ሊፈራና ሊከበር ይገባዋል፡፡ በምሳሌ 1፡7 "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው"፡፡ ይላል፡፡ ይህ መጀመሪያ የሆነበት ምክንያት ምናልባት ከመውደድ ይልቅ መፍራት ቀላል ስለሆነ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ጌታን ስንፈራ፡-

1. የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ኃያልነት መቀበላችን ነው፡፡
2. ጌታ እኛ በምንሠራው ሥራ ሁሉ ውስጥ እንደሚያገባው ማወቃችን ይሆናል፡፡
3. ለመታዘዝ ውሳኔ መወሰናችንንም ይገልጻል፡፡ ከላይ የተገለጸው ፍርሀት ጤናማ የሆነ አክብሮትና መገዛትን ለመግለጽ ታስቦ ነው፡፡

በሌላ በኩል አምልኮ ከአገልግሎት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ እግዚአብሔር አምላክህን ብቻ አምልክ እርሱንም ብቻ አገልግል፡፡ እነዚህ ሁለት ትዕዛዞች ታዲያ የተለያዩ አይደሉም እግዚአብሔርን ማገልገል ማለት ምን ማለት ነው? መጽሐፍ ቅዱስ አገልግሎትን በሁለት መንገድ ይገልፀዋል፡፡

- ✓ አንደኛው መታዘዝን ሲያመለክት እርሱ የሚለንን በማድረግ እናገለግለዋለን፡፡ ልክ ባሪያ የጌታውን ትዕዛዝ እንዲሚፈጽም እርሱ የሚለንን በማድረግ እናገለግለዋለን፡፡
- ✓ የአገልግሎት ሌላኛው መልክ ወደ መቅደስ በመሄድ በሚደረገው ስነ-ስርዓት መሳተፍን ያመለክታል፡፡ መዝሙረኛው "በመዝሙር እግዚአብሔርን በደስታ አገልግሉ" ይለናልና፡፡ መዝ 100፡2 ደግሞ በፊቱ ኑና ዘምሩ ይለናል፡፡

ስለዚህ

- አምልኮ ለእግዚአብሔር የሚገባ ነው፡፡
- አምልኮን ለመፈጸም ዋጋ ያስከፍላል፡፡
- አምልኮ ስግደትን ያካትታል፡፡
- አምልኮ ስጦታንም ይጨምራል፡፡
- አምልኮ በጌታም ሆነ በሰይጣን እጅግ ይፈለጋል፡፡
- ሊመለክ የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡
- አምልኮ እግዚአብሔርን በመፍራትና በማክበር ሊፈጸም ይገባዋል፡፡

- **አምልኮ እግዚአብሔርን ማገልገልም ነው።**

**ስናጠቃልለው፡-** *አምልኮ ሰው ለፈጣሪውና ለአምላኩ ስለአምላክነቱና ስላደረገለትም የማዳንና የቸርነት ሥራ ምስጋናን አድናቆትን አክብሮትንና አገልግሎትን ማቅረብ ነው። በዚህም የአምላኩን ታላቅነትና ለአምላኩም ያለውን ተገዥነት እንዲሁም በእርሱ ላይ ያለውን መደገፍ የሚገልጽበት መንገድ ነው።*

# ምዕራፍ ሁለት

*"በፊቱ የተገለጠ መልካም ማንነት ሳይኖርህ በአምልኮህ የእግዚአብሔር ፊት አይገለጥልህም"*

## 2. የአምልኮ ታርካዊ ዳራ (አመጣጥ)

አምልኮን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ስናጠናው ታሪካዊ ዳራ ያለውና የሰው ልጅ እግዚአብሔር በገለጠለት መጠን በግልም ይሁን በሕብረት በተለያዩ ቦታም ይሁን በተወሰነ ስፍራ አምላኩን ከፍ ከፍ የሚያደርግበት ፍጡራዊ ምላሽ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ ይህንን ሃሳብ ያሳየናል፡፡ በመቀጠል ታሪካዊ ዳራውን ከሙሴ በፊት፣ በዘመነ ሙሴ፣ በሙክራብ አምልኮ ወቅት፣ በጥንቷ ቤተ-ክርስቲያንና በዘመነ ጳውሎስ ድረስ በአጭሩ እንመለከታለን፡፡

## 2.1. አምልኮ ከሙሴ በፊት

መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስንመረምር ከሙሴ በፊት የነበሩ ቅዱሳን ከእግዚአብሔር ምሪት በመቀበልም ሆነ በራሳቸው መነሳሳት እግዚአብሔርን በልዩ ልዩ መንገድ ያመልኩ እንደ ነበር እናስተውላለን፡፡በዘፍ 8 እና 9 ላይ ኖህ ለእግዚአብሔር መልካም መዓዛ ሽታ ያለውን መስዋዕት በማቅረቡ እግዚአብሔር እርሱንና ቤተሰቡን እንደባረከ እንመለከታልን፡፡አብርሃም በሴኬም፣ በቤቴል፣ በሄብሮንና በሞሪያ ተራራ ላይ መስዋዕት በማቅረብ እግዚአብሔርን እንዳመለከ፣ይስሐቅ በቤርሳቤህ መሰዊያ እንደሰራና እንደፀለየ፣ ያዕቆብም በቤቴል የድንጋይ ሐውልት በማቆምና ዘይት በማፍሰስ እግዚአብሔርን እንዳመለከ እናስተውላለን፡፡ መሰዊያንም በቤቴልና

በሴኬም አቁሞ እንዳመለከ እናያለን፡፡ እንግዲህ ከዚህ ሁሉ የምንረዳው እነዚህ ግለሰቦች፡፡

1) አንዳቸውም ካህን እንዳልነበራቸውና ራሳቸው የየግላቸውን መሰዊያ በማቆም እንስሳትን ሰውተው እንዳመለኩ የቤቱ መሪ የአምልኮውም መሪ እንደነበረ እናያለን፡፡
2) አባቶች ስላከናወኑት አምልኮ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ብዙ መመሪያ እንዳልነበረ፣ ልዩ የአምልኮ ቀንም ሆነ ወቅት እንዳልተደነገገ ሆኖም እግዚአብሔርን ብቻ በፈለጉት ቦታ፣ በፈለጉት ዓይነትና ጊዜ እንዳመለኩ እናስተውላለን፡፡
3) ብዙ የአሠራር መንገድ እንዳልነበረ፡፡ ሆኖም ወይን ወይም ዘይት መሰዊያው ላይ በማፍሰስ ከፊሉን በመብላት አምልኮ ያካሂዱ እንደነበር እንገነዘባለን፡፡

ለአቤል፣ ለኖህ፣ ለአብርሃም፣ ለያዕቆብ ጊዜ ስፍራና መመሪያ አምልኮአቸውን አይወስንም ነበር፡፡ ለሁሉም ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ የሚል ነበር፡፡ እግዚአብሔር ስለሚገባው መቶ በመቶ ብቻውን መመለክን ይሻ ነበር አስፈላጊውም ይህ ነበር፡፡

*<u>አንድ ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ ልንገራችሁ፡-</u>*

*ንግስት ኤልዛቤል አምልኮተ ባዕድ ወደ ሀገርዋ ወደ እስራኤል እንዲገባ አደረገች፡፡ ሕዝቦችዋም እስራኣላዉያን እግዚአብሔርን ትተው የርስዋን ጣዖት በዓልን ማምለክ ጀመሩ፡፡ ንጉሣቸው አክዓብ ግን ይህን ለመከለክል ምንም እርምጃ አልወሰደም፡፡ እግዚአብሔርም በህዝቡ ላይ ጽኑ ረሃብ አመጣ፡፡ (ጌታ መቼም ወደ እርሱ እንድንመለስ ሲፈልግ ችግር እንዲመጣብን ያደርጋል፡፡) በእርሱ እንድንታመን ፈልጎ ነው፡፡*

*አንድ ረሃብ ባጠቃው አገር አንዲት ባልዋ የሞተባት ሴት ከልጅዋ ጋር ትኖር ነበር፡፡ በሀገሩ ለኢያሌ ወራት ዝናብ አልጣለም ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ጽኑ ረሀብ ነበር፡፡ ለሷም የቀረው ምግብ ጥቂት ነበር፡፡ ይህች ባልቴት የነበራት ጥቂት ዱቄትና ዘይት ብቻ ነበር፡፡ ይህችን ያላትን ለመጋገር እንጨት ለቀማ ሄደች፡፡ እንጨት ስትለቅምም ነብዩ ኤልያስ አገኛትና " ውሃና ትንሽ የሚበላ ይዘሽ ነይ" ብሎ አዘዛት፡፡ እስዋም " ያለኝ ጥቂት ዱቄትና ዘይት ነው ይህችን ከልጄ ጋር በልተን መሞት ብቻ ነው ያለን እድል" አለችው፡፡ ኤልያስም፡- "ኢይዘሽ አትፍሪ በቅድሚያ ለእኔ ጋግሪ ከዚያ ለአንቺናለልጅሽ ጌታ ዝናብ እስኪያዘንብ ዱቄትሽና ዘይትሽ እንዳይልቅ ቃል ገብቶአል" አላት፡፡ባልቴቲቱ ነብዩ ያላትን አመነች ስለዚህ ከእርሱ ጋር ምንም አልተከራከረችም፤ ብቻ ሄዳ ለኤልያስ ትንሽ ዳቦ ጋገረችለት፣ ይገርማችኋል፤ እግዚአብሔር ዝናብን እስኪልክላቸው ድረስ ለራስዋና ለልጅዋ የሚበቃ ነበራት፡፡ የዚያች ባለቤት ልጅዋ ታሞ ሞተ ባልቴቲቱ ኤልያስን፡- እግዚአብሔር ስለኃጢአቴ ነው የሚቀጣኝ? ብላ ጠየቀች ኤልያስም ፀለየ እግዚአብሔርም ልጁን እንደገና በሕይወት እንዲኖር አደረገው፡፡*

እግዚአብሔር ችግር እንዲመጣብን የሚፈቅደው እንዲያው ሊቀጣን ፈልጎ አይደለም፡፡ ወደ እርሱ በይበልጥ እንድንቀርብ እርሱን ማምለክ በሚገባ እንድንጨምር ብሎ እንጂ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የሰወርነውን ኃጢአታችንን ሊያሳስብን ይፈልጋል፡፡ አሁንም እንዲህ የሚያደርገው ለኛው ጥቅም ብሎ ነው፡፡ ከርሱ ጋር ህብረት ቢኖረን የበለጠ ደስተኞች እንደምንሆን ያውቃልና ከእርሱ ጋር ያለን ህብረት ደግሞ ኃይሉን ይገልጽልናል፡፡

ወንድሞቼ ዛሬ የተለያየ ችግር፣ ረሃብ፣ ማጣት የሚደርስብን እግዚአብሔርን ማምለክ ወይም የአምልኮ ሕይወት ወደዚያ እንዲጨምር ነው እንጂ ወደ ኋላ እንድናፈገፍግ አይደለም፡፡

- *ማሳሰቢያ*፡- መከራ፣ ችግር፣ ማጣት፣ ረሃብ ለእኛ መኖሪያ ቦታ ሳይሆን በዚያ መካከል ተፈትነን የምናልፍበት መሸጋገሪያ ነው፤ የምታልፉትን ሳይሆን የምታዩትን ያንኑ ትወርሳላችሁ፡፡

## 2.2. ሙሴና የማደሪያ ድንኳን

በሙሴ ዘመን አምልኮ ቀለል ካለ የአፈጻጸም ሂደት ወደ ዝርዝር መመሪያና መዋቅር አዘል ተለወጠ፡፡

እግዚአብሔር አምላክ በጥልቅና በዝርዝር

1) መስዋዕት መቼ መደረግ እንዳለበት
2) እንዴት መደረግ እንዳለበት
3) የት መደረግ እንዳለበት
4) ማን ማድረግ እንዳለበት በግልፅ አስቀመጠ፡፡

ከዚህም የተነሣ አምልኮ መደበኛና ደንብ አዘል ሆነ፡፡ እናም በሙሴ ህግ የተቀደሱ ቦታዎች፣ የተቀደሱ ሰዎች፣ የተቀደሱ እንስሳት፤ የተቀደሱ ኃይማኖታዊ ስርዓትና የተቀደሱ ዕለታት ነበሩ፡፡ የማደሪያውን ድንኳን ብንወስድ አደባባዩ ቅዱስ፣ ቅድስተ ክፍሉ በጣም ቅዱስ፣ ቅድስተ ቅዱሳኑ እጅግ በጣም ቅዱስ እንደ ነበሩ እንገነዘባለን፡፡ ወደ እግዚአብሔርም በተፈለገው ጊዜ አይቀረብም ነበር፡፡ ስግደት አምልኮው በተቀደሰ ሰው በታቀደ ጊዜ፣ ወደ ተቀደሰው ስፍራ በተቀደሰ ስርዓት አፈጻጸም መሆን ነበረበት፡፡ እንግዲህ የማደሪያው ድንኳን የእግዚአብሔርን ቅድስና በግልጽ የሚያሳይ ነበር፡፡ ሆኖም ግን

እግዚአብሔር ከሕዝቡ የራቀ አልነበረም፡፡ በማደሪያው ድንኳን በሕዝቡ ሰፈር ነበር፡፡

በጥንቷ እስራኤል በማደሪያው ድንኳን በእግዚአብሔር ጥሪ ሊያመልኩ የተቀደሱ (የተለዩ) ሌዋዊያን የሚባሉ ሰዎች ነበሩ፡፡ የተቀደሱ እንስሳትን ዕፀዋት ነበሩ፡፡ የበኩር ምርት ለእግዚአብሔር የተለየ ነበር፡፡ የተለየ ዕጣንም ነበር፡፡ በቀናት፣ በሳምንት፣ በዓመት፣ በአምሳ ዓመታት ውስጥ ለአምልኮ የተለዩ ቀናት ነበሩ፡፡ ህልየት (ሙዚቃም) የተለየ ነበር፡፡ ዝርዝር የአምልኮ ሕግጋቱና የነበራቸው ዓላማ አንድና አንድ ብቻ ነበር እርሱም እግዚአብሔርን ማክበር ነው፡፡

አምልኮ በብሉይ ኪዳን አክብሮትንና ታማኝነትን ለእግዚአብሔር የምንገልጽበት ድርጊቱ ሲሆን የሚከናወነውም በተወሰነ ቦታና በታቀደለት ጊዜ ነበር፡፡ ለምሳሌ ያህል ኢየሩሳሌም የአይሁዳውያን የአምልኮ ማዕከል ነበረች (ዮሐ4፥20) ዳንኤልን ለአብነት ያህል ብንወስድ የእልፍኙ መስኮቶች በኢየሩሳሌም አንጻር ተከፍተው በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ይፀልይና ያመሰግን ነበር (ዳን 6፥10) በተጨማሪም በቤተመቅደስ (መዝ 138፥2) በመሰዊያው አካባቢ (1ኛ ነገ 18፥ 22, ኢሳ 36፥7) ኤር 7፥2)

## 2.3. የምኩራብ አምልኮ፡-

ቤተ-መቅደሱ ከተደመሰሰና አይሁዳዊያንም በመካከለኛው ምስራቅ ከተበታተኑ በኋላ አዲስ የአምልኮ ስርዓት በምኩራብ ተጀመረ፡፡ የትኩረት አቅጣጫውም መስዋዕት ላይ ሳይሆን ቅዱሳት መጽሐፍት ላይ ነበር፡፡ የምኩራብ አምልኮ በፀሎት፣ ምስጋናን፣ መንፈሳዊ ትምህርትንም ሆነ ስብከትን ሳያካትት ማህበራዊ ኑሮም አንድ ክፍል ነበር፤ ለአብነት ያህል የአምልኮውን ይዘት (ነህ 8፥4-6) እንመለከት፡- *"… ዕዝራም በሕዝቡ*

*ሁሉ ላይ እያዩ መጽሐፉን ገለጡ፤ በገለጠውም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ቆመው ዕዝራም ታላቁን አምላክ እግዚአብሔርን ባረከ፤ ሕዝቡም ሁሉ እጃቸውን እየዘረጉ፡፡ አሜን፣ አሜን ብለው መለሱ፡፡ ራሳቸውንም አዘነበሉ በግምባራቸውም ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ..."*

## 2.4. ሙዚቃ በቤተመቅደስ

ዳዊት ከልጅነቱ ጀምሮ የሙዚቃ ልምድ እንደነበረው ከታሪኩ እናነባለን፡፡ የአባቱን በጎች በሚጠብቅበት ጊዜ ሙዚቃ እየደራሰ በክራርና በዝማሬ አምላኩን ያመሰግን ነበር፡፡ የመዝሙሮቹ ስምም በግሪኩ "ሳሎ" ይባላል፡፡ ይህም ማለት በነጠላ አውታር ሙዚቃን መደርደር ማለት ነው፡፡ ንጉስ ከሆነም በኋላ ከፊሎቹን ሌዋዉያን በሙዚቃ መሳሪያ የአምልኮ መሪ አድርጓቸው እንደነበር እናስተውላለን፡፡ (1ዜና 23፡5, 25፡1-8)

ስለሆነም ሙዚቃ ከቋሚ የአምልኮ መሳሪያዎች እንደሆነ ተቆጠረ፡፡ ለአብነት ያህል መዝ 150ን ብንወስድ *"እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት፤ በኃይሉ ጠፈር አመስግኑት፣ በችሎቱ አመስግኑት፣ በታላቅነቱ ብዛት አመስግኑት፣ በመለከት ድምጽ አመስግኑት፣ በበገናና በመሰንቆ አመስግኑት፣ በከበሮና በዘፈን አመስግኑት፣ በአውታርና በእምቢልታ አመስግኑት፤ ድምፁ መልካም በሆነ ጸናልጽል አመስግኑት፣ እልልታ ባለው ጸናጽል አመስግኑት፣ እስትንፋስ ያለ ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን ሃሌሉያ"* ይላል፡፡

*እዚህ ጋ አንድ አጭር ታሪክ ልንገራችሁ፡-*

*የአዝመራው አያያዝ ተሰፋ የሚያስቆርጥ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት አቶ በቀለና ባለቤቱ ወይዘሮ ገነት ስጋት ያዛቸው፡፡ "ልጆቻችንን ምን እናበላቸው ይሆን?" ይሉም ጀመሩ አንድ ቀን እግዚአብሔር አባታችን ሆይ ዘንድሮ በቂ ልብሰ ከሰጠኸን የምስጋና መግለጫ አድርገን አንድ በግ*

*ለቤተ-ክርስቲያን እንሰጣለን፡፡ አስራታችንን ለመስጠት ቃል እንገባልሃለን፡፡" ብለው ፀለዩ፡፡ እነሆም የመከር ጊዜ መጣ በቂ ሰብልም አገኙ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ፡፡ ዳሩ ግን አቶ በቀለ ኮት አስፈለገውና እሱን ለመግዛት በጉን ሸጠው ምንም እንኳ ሳንቲማቸውን በምጽዋት መሰብሰቢያ ጣል ጣል ቢያደርጉም አሥራታቸውን መስጠት ቸል አሉ፡- አዬ ጉድ! ጌታን እንዲህ ይዋሹት! ያታልሉት! ዳሩ ግን ምን ይደረግ መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልብ ተንኮለኛ ነው ብሎ የለምን?*

- *ማሳሰቢያ፡- እኛ እግዚአብሔርን ስናመሰግን የአየር ጠባይ ማየት የለብንም መጽሐፍ ቅዱሳችን እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን ካለ የምን ማጭበርበር ነው ውድ አንባቢያን ሆይ ምንም ነገር በሌለበት በምድረ በዳ እግዚአብሔርን ማመስገን ጀምር ስታመሰግን ጎደሎህ ይሞላል፡፡*

" የእኛ አምላካችን ሁሉን ያደረገ ግን ያልተደረገ አምላካችን ነው ! "

## 2.5. ጌታ ኢየሱስና አምልኮ

ጌታ ኢየሱስ ያደገው በገሊላ በመሆኑ ወደ ኢየሩሳሌም በስርዓት ቅዳሴ ወቅት ቢሄድም የአምልኮ ጊዜውን ያዘወትር የነበረው ከቤተመቅደስ ውጭ በግልና በሕብረት ነበር፡፡ ስለአምልኮ በአመርቂ ሁኔታ የገለጸበትን አገላለጽ በግጥም ልንገራችሁ፡፡ በዮሐ 4፡1-23

*በየቀኑ እየተጓዘች ረጅም መንገድ*
*እንስራ ተሸክማ ወደ ያዕቆብ ጉድጓድ*
*ማያሳርፍ ውሃ ከጉድጓ ልትቀዳ*
*እየተመላለሰች የዛለችው ጌታን ሳትረዳ*
*ሁለመናዋን ለባዕድ ነገር በከንቱ አስገብራ*

*የህይወት ውሃ እንደሚሰጣት ሳታጣራ*
*ኢየሱስ መሆኑን ሳታውቅ መድኃኒት*
*በብዙ ጉዳይ የተከራከረችው ሳምራዊት ሴት*
*እውነቱ ስገባት ተማርከ ልቧ በጌታ*
*ስለኢየሱስ ዝና መሰከረች በደስታ*
*ከህይወቷ ሰውነቷ የከበባት ጨለማ*
*ዳነ በሷ ምክንያት የሳምራዊያን ከተማ*
*ጆሮዋ ሰምቶ አዲስ ዜና ሲደረግላት ድንቅ*
*እንቆቅልሿ በኢየሱስ መፈታቱን ስታውቅ*
*የሕይወት ውሃ ከሆዷ ሲፈልቅ*
*በረሃ ሕይወቷ ሲለመልም ፈነጠዘች በሳቅ*
*ኢየሱስ ሲደርስላት ረሳች የመከራ ስንቅ*
*ጌታን የቆጠረችሁ እንደጠላት*
*ሀሳቡን የተቃረነችሁ በዚያን ዕለት*
*ለብዙዎች ሆነች የመዳን ምክንያት*
*ከርኩሰት ሥራ በፍፁም ልቧ ርቃ*
*የዓለምን ግብዣ ስለጌታ ብላ ንቃ*
*አፏ ሳይሆን ህይወቷ ብቻ ለሎችን አነቃ*
*ኢየሱስ መሆኑን የሰላም አለቃ*
*ብዙ ሰው አሳወቀች ለራሷ አውቃ*

ዕብ 22፥28 እንደሚጠቁመን እግዚአብሔርን የምናመልከው ለእርሱ ደስ በሚል መንገድ እንጂ በራሳችን መንገድ አይደለም፡፡ *"ስለዚህ የማይናወጥ መንግስት ስለምንቀበል በማክበርና በፍርሃት እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ፀጋ እንያዝ"* እርሱ ደስ የሚሰኝበትን

*መንገድ የሚነግረን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። (… የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።)*

በመንፈስ መስገድ ማለት ከእርሱ ጋር ግንኙነት ማድረግ እንድንችል በተሰጠን መንፈሳችን ምላሽ መስጠት ነው። አምልኮ መንፈሳችን ለእግዚአብሔር መንፈስ መልስ የሚሰጥበት ሁኔታ ነው። አምልኮ በእግዚአብሔር ደስ የመሰኘት ነገርም ስለሆነ ስሜቶቻችንንም ይጨምራል። ማለትም እግዚአብሔር ስሜቶቻችንን የሰጠን በማስመሰል ሳይሆን በጥልቀት እንድናመልከው ነው። በእውነት መስገድ (ማምለክ) ማለት እግዚአብሔር ለግላችን በሰጠን ልምድና ባህሪ ለርሱ ያለንን ፍቅር በእውነት መግለጽ ማለት ነው።

## 2.6. የጥንቷ ቤተ-ክርስቲያን፡-

በሐዋሪያት ስራ 2፣41-42 *"ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ በሐዋሪያትም ትምህርትና በህብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየፀሎቱም ይተጉ ነበር።"* ይህ ድርጊት ጌታ ላደረገላቸው አምልኳዊ ምላሽ ነው። በይበልጥ ቁጥር 46-47 እንደዚህ ተገልጿል።

*"በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቀረቡ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውንም ይመገቡ ነበር። እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በህዝብ ሁሉ ሞገስ ነበራቸው ጌታም የሚድኑትን እለት እለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።"*

## 2.7. አምልኮ በጳውሎስ ዘመን፡-

ሐዋሪያው ጳውሎስ እንደገለፀው (ሮሜ 12፣1) አምልኮ ሁለንተናን ለጌታ መስጠት ነው። ባስተሳሰባችን፣ በስሜታችን ለጌታ ክብር ስንኖር ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ተገዛን ማለት ነው። ይህም እውነተኛ አምልኮ

ይባላል፡፡ አገልግሎታችን በቤተመቅደስና በጊዜ አይወሰንም የትም ቦታና መቼም ልናገለግል እንችላለን፡፡ ምክንያቱም እኛው ራሳችን ቤተመቅደስ ነንና፡፡

ሐዋሪያው በሮሜ 15፥16 ም *"ነገር ግን አሕዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀደሰው የተወደደ መስዋዕት ሊሆኑ ለእግዚአብሔር ወንጌል እንደ ካህን እያገለገልሁ፤ ለአህዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ እሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ ምክንያት ተመልሼ ላሳስባችሁ ብዬ በአንዳንድ ቦታ በድፍረት ጻፍሁላችሁ"* በማለት ማገልገል ራሱ አንዱ የአምልኮ ዓይነት እንደሆነ ይገልፃል፡፡ በሮሜ 35፥22 መሰረት ደግሞ ቁሳዊ እርዳታ ማድረግ ወይም የገንዘብ እርዳታ መስጠት አንዱ እግዚአብሔርን ማምለኪያ መንገድ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

*"በሰማይ የሞላው የእግዚአብሔር ክብር በምድርም ሞልቷል፣ አምልኮህ ወደዚህች ክብሩን ወደተሞላች ምድር መድረስ ይሁንልህ።"*

## 3. የክርስቲያን አምልኮ ልምምድ

ክርስቲያኖች በየሳምንቱ ለአምልኮ በጎጆ ቤት፣ በልዩ ቅርጽ በተሰሩ ካቴድራሎች በእስር ቤቶችና በአረጋዉያን መጦሪያ ማዕከል፣ በሕንፀዎችና በመንደር አደባባዮች፤ እንደዚሁም ገዘፍ ተደርገው በተሠሩ ትላልቅ የአምልኮ አዳራሾች እና በገጠራማው አካባቢ በሚሰሩ የአምልኮ መጠለያዎች ሳይቀር ይሰበሰባሉ።

በዚህ ዓይነት የተለያየ አውድ የሚካሄድ አምልኮ ይዘቱም እንደዛው ልዩ ልዩ እንደሚሆን አይካድም። አንድንድ ማህበረ ምዕመናን በጥንቃቄ ተጠንቶ የተዘጋጀ ስብከት ያዳምጣሉ ሌሎች ደግሞ ያለምንም ዝግጅት በስሜት የታጀበ ስብከት ይሰበካሉ አንዳንድ አጥቢያዎች የሮክ ባንድ በመሰለ ሙዚቃ ታጅበው ይዘምራሉ። አንዳንዶች ደግሞ በጥንታዊ ትላልቅ ፒያኖች ይታጀባሉ ሌሎች ደግሞ ከባንድ ጋር በመሆን በአስመላኪዎች ይታጀባሉ አንዳንዶች ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ይጠቀማሉ ሌሎች ደግሞ ምንም አጃቢ ሳይኖራቸው ያምልካሉ።

አለባበስንም በተመለከተ አንዳንዶች ለእሁድ አምልኮ ተገቢ የመሰላቸውን አለባበስ ለብሰው ያመልካሉ። ሌሎች ደግሞ ባህር ዳር ለሽርሽር እንደሚሄድ ሰው ግድ የለሽ አለባበስ ለብሰው ለማምለክ ይመጣሉ።

ይሁን እንጂ የተለያየ ባህላዊ አገላለጾችና የአምልኮ ዓይነቶች ቢኖሩም ቅሉ ከባህል በላይ ለክርስቶስ ወንጌል ታማኝነትን የሚያስጠብቁ በዛ ያሉ ሁሉንም ዓይነት የክርስቲያን አምልኮ የሚመለከቱ ልማዶች አሉ።

በተለይም ትውልድ በማያቋርጥ በልዩ ልዩ የአምልኮ ሥርዓቶች ላይ ትከሩት በሚያደርግበት በዚህ ዘመን መሪዎች እንደልማድ ሊተጉበት የሚገባ ዋና ነገር ቢኖር ከባህል ያለፈ መደበኛ የሆነ የክርስቲያን አምልኮ መስፈርት የሚያሟላና በንቃት በታማኝነት አምልኮን ለሚለማመዱ ማህበሮች መፈጠር ምክንያት ሊሆኑ ይገባል፡፡

ለእነዚህ መሠረታዊ የአምልኮ መስፈርቶች ትኩረት ያለመስጠት፣ ለእውነተኛ የቃሉ አገልግሎት አለመትጋት፣ መሠረታዊ የሙዚቃ ስልትን ያለመጠቀም፣ እና ትክክለኛ የአምልኮ ሥርዓትን አለመቅረጽ ለክርስቲያን ሕይወት ተስፋ ከሆነው የክርስቶስ ወንጌል ፈቃድ ሊያርቅና መሰናክል ሊሆን ይችላል፡፡ ባህል ዘለል የሆኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ትላልቅ መጽሐፍትን መፃፍ ይቻል ይሆናል ይሁን እንጂ በዚህ ጽሁፍ ላይ በተጠቀሱት አጫጭር መረዳቶች ደግሞ ሁሉንም ዓይነት የክርስቲያን አምልኮ መድረኮችን በሚመለከት በበቂ ሁኔታ ጭብጥ ሊሰጡ የሚችሉ ሁነኛ ሀሳቦች ይገኛሉ፡፡

1) የክርስቲያን አምልኮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊሆን ይገባል

መጽሐፍ ቅዱስ ስለእግዚአብሔርና ክርስቶስ ስለዋጃት ዓለም መረዳት እንዲኖረን ዋና የእውቀት ምንጭ ነው፡፡ ስለዚህ አምልኮ ሁነኛ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ሊታጀብ ይገባል፡፡ እንደዚሁም አምልኳችን የእግዚአብሔርን አምላክነት፣ ባሕሪውንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮትን ማካተትና መሳል ይጠበቅበታል፡፡

በአምልኮ ላይ የሚገለጡ ልምምዶችን በተመለከተም ደግሞ በግልጽ ለተቀመጡት መፅሃፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዞች የሚገዛና ስለተሳሳተ አምልኮትም በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ ለተገለጡት ማስጠንቀቂያዎች ችላ የማይል ወይም ትኩረት የማይነፍግ ሊሆን ይገባል፡፡

አምልኮ በዋነኛነት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ላይ እና በፍጥረት ሁሉ ላይ አዳኝነቱን ሊገለጥ ስላለው የእግዚአብሔር መንግስት ከመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በመገለጥ ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባዋል።

2) የክርስቲያን አምልኮ እግዚአብሔርም ሰውም የሚናገርበት የሁለትዮሽ ግንኙነት እና ሀብረት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባዋል።

በአምልኮ ወቅት እግዚአብሔር ይናገረናል ደግሞ ይሰጠናል። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት አምላካችን ይገስጸናል፣ ያጽናናናል፣ እንደዚሁም ያነቃቃናል። እኛ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ መረዳትን እያደመጥን በምስጋናና በንስሐ፣ በምልጃ፣ እንዲሁም በምስክርነት ምላሽ እንሰጣለን።

እግዚአብሔር በማያቋርጥ መልኩ ሕዝቡን በመቀስቀስና ከሕዝቡ ጋር ግንኙነት በማድረግ እንደሚሠራ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ከእግዚአብሔር ጋር ጤነኛ ግንኙነት ሲኖረን ሚዛኑን ወደጠበቀና በአትኩሮት ወደ ማዳመጥና እውነትን ወደ መናገር ልምምድ ውስጥ እንገባለን። ጤናማ አምልኮ ልክ እንደዚሁ ነው። ለዚህም ነው በአምልኮ ላይ የቃላችን ትክክለኛነት ግድ የሚለው። እግዚአብሔር ጉባኤዉን ለመናገር ቃሎቻችንን ይጠቀምባቸዋል። እኛ ደግሞ በቃሎቻችንን ምስጋናችንንና ፀሎታችንን ወደ እግዚአብሔር እናቀርባለን።

3) የክርስቲያን አምልኮ በቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተ ነው።

በአምልኮ የእግዚአብሔር መልካምነትና ከእኛ ጋር በክርስቶስ በኩል የገባው አዲሱ ቃል ኪዳን ታድሷል፣ ታውጆአል፣ ታትሟል። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ሊኖረን ወደሚገባ መልካም ሕብረት የጠራን በሚያስገድድ የውል ስምምነት ሳይሆን ራሱን በፍቅር አሳልፎ በሰጠ፣ ተስፋ እና እምነት ላይ በተመሰረተ ቃል ኪዳናዊ ሕብረት ነው እንጂ ይህም እንደ

ሕጋዊ የውል ስምምነት ሳይሆን እንደ ጋብቻ ቃል ኪዳን ስምምነት ዓይነት ነው፡፡

አምልኮ የእግዚአብሔርን ተስፋ የምናስተውልበትና ራሳችንንም ለቃል ኪዳናዊ ግንኙነታችን አሳልፈን የምንሰጥበት ነው፡፡ በማንኛውም የአምልኮ አገልግሎት መታሰብ የሚኖርበት ጉዳይ ቢኖር አምልኮው እንደ ታማኝና ቃል ኪዳኑን እንደጠበቀ ወዳጅ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር የሚያስችል ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

4) የክርስቲያን አምልኮ የሥላሴን ትምህርት መሠረት ያደረገ ሊሆን ይገባዋል፡፡

በአምልኮአችን ልንደርስ የሚገባው በአንድነቱና በሦስትነቱ ታውቆ የሚኖረው እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ እርሱም በመለኮት አንድ በአካል ሦስት የሆነው ቅዱስ አምላክ፣ የፍቅር አምላክ፣ ውብ አምላክና ኃይለኛ አምላክ ነው፡፡

በፀጋው ወደ አምልኮ የሚጋብዘንና ምላሻችንንም የሚያደምጠው እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡ ፍጹማን የሚያደርገን ምስጋናችንና ልመናችንንም የሚሰማልን በሰማነው ላይ መረዳት እንዲኖረን የሚያግዘንና ምላሽ ደግሞ እንድንሰጥ የሚያበረታታን እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡ እንግዲህ በአምልኮ ሕብረት እንድናደርግ የምንጋበዘው ከእግዚአብሔር አብ ጋር በእግዚአብሔር ወልድ በኩልና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው፡፡

አምልኮ እንዲሁ ቁሳዊ በሆኑ ነገሮች አማካኝነት ለምሳሌ፡- በጥምቀተ ውሃ፣ በሕብስትና በወይን፣ ደግሞም በሙዚቃ ቃና፣ በሕብረት በሰውነት እንቅስቃሴ፣ በፈገግታ እና ሰላምታ በመለዋወጥ ሳይቀር በአንድነትና በሦስትነት ወደ ሚመለከው እግዚአብሔር ቀርበን የምንገባበትና የምንካፈልበት ሥርዓት ነው፡፡

በአምልኮአችን ትኩረት የምናደርገው ራሱን አሳልፎ በሰጠን በእግዚአብሔር ላይ ነው። ይህ እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ አምልኮ እንቅስቃሴዎቻችን ላይ ብቻ በማተኮር እንዳንወሰድ ይጠብቀናል።

5) የክርስቲያን አምልኮ ማህበራዊ ነው።

የክርስቶስ ወንጌል ከሌሎች ሰዎች ሕብረት እንዲኖረን አስችሎናል። አምልኮ የቤተ-ክርስቲያንን እምነት በተግባር የምንገለጽበት አንድነታችን ቅድስናችንና የቤተክርስቲያን ምስክርነትን ጎልቶ የሚታይበት ጥልቀቱም የሚለካበት ነው። አጽንኦት ሊሰጠው የሚገባ ነገር ቢኖር በአምልኮ በሚያስደንቅ ሁኔታ የተለያየ ማንነት ያላቸው ሰዎች በአንድነት ያመስግናሉ በአንድነት ይጸልያሉ በአንድነት እግዚአብሔርን ይሰማሉ በአንድነት ቃል ኪዳን ደግሞ ይገባሉ። ስለዚህ አምልኮ የሁላችንም አስተዋጽኦ ውጤት ነው።

6) የክርስቲያን አምልኮ ለሌሎች የሚራራ የሚጠነቀቅና ሌሎችን የሚጋብዝ ሊሆን ይገባዋል።

የክርስቲያን አምልኮ በክርስቲያኑ ላይ ብቻ ያተኮረ ሊሆን አይገባም። አምልኳችን ለዓለም ሁሉ መፀለይ እንዲሁም ደግሞ በፍርሃት ያሉትን፣ የሚጨነቁትና በብቸኝነት ለሚኖሩት ሁሉ ርህራሄን ማሳየት ይጠበቅበታል። የሕብረት አምልኮ ሌሎችን እንድናገለግል ምስክር እንድንሆን በአምልኮ ሕይወት እንድንኖርና ወደ ሌሎች ደግሞ እንድንላክ የሚያደርገን ነው።

አምልኮ በወንጌል ተስፋዎች የሚያጽናናን ብቻ ሳይሆን ይህ ዓለም ምን ያህል የተበላሸና በፍርሃት የተሞላ እንደሆነና ምን ያህል አዳኝ እንደሚያስፈልገው እንድንገነዘብ በማድረግ ሃላፊነት እንዲሰማንም የሚያደርግ ነው። አምልኮ ይህ የወደቀው ዓለም ከጥፋት እንዲድን እንድናገለግል የልባችንን መሻት የበለጠ የሚያቀጣጥል ነው።

7) የክርስቲያን አምልኮ “በአለም ውስጥ ነገር ግን ከአለም ያልሆነ” ሊሆን ይገባዋል፡፡

የክርስቲያን አምልኮ ሁልጊዜ ባህልን ያንፀባርቃል፡፡ የንግግር ዘይቤው፤ አለባበሱ፣ የስርዓት አጠቃቀሙ፣ የሕይወት ልምምዱና የሙዚቃ ውህደት እና ስዕላዊ መገለጫዎች ሁሉ እንደ የባህሉ አውድ ይለያያሉ፡፡ ይህ እንዲህ ቢሆንም አምልኮ በባህል ተጽዕኖ ውስጥ ሊወድቅ አይገባም፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል ከባህል በላይ በመሆን የነብይነት ተግባሩን ሊፈጽምና ተገቢ ያልሆኑ ባህሎችንም ሊኮንን ይገባዋል፡፡

8) የክርስቲያን አምልኮ በለጋስነት ፍጹም በሆነ ሁኔታ እኛነታችንን በእግዚአብሔር ፊት የምናፈስበት ሊሆን ይገባል፡፡

አምልኮ አሰልቺና አድካሚ መሆን የለበትም፡፡ ይልቁንስ ልክ እንደዛዉ በጌታ በኢየሱስ እግር ላይ እንደፈሰሰው ሽቶ የሚያውድ መዓዛ ያለው መሆን አለበት፡፡ አምልኳችን ለፈጠረንና ላዳነን አምላካችን ከልብ በመነጨ ፍቅርና ምስጋና ዝማሬ ያለመቆጠብ የሚቀርብ ሊሆን ይገባዋል፡፡ አምልኮ ምርጥ የሆነውን ነገራችንን ለእግዚአብሔር እንድንሰዋ ነው የሚጋብዘን፡፡

መዘመር ስንለማመድ ቃሉን ለመስበክ ስንዘጋጅ ገንዘባችንና ጊዜያችን መስዋዕት አድርገን ለእግዚአብሔር ለመስጠጥ ጭምር የሚደረግ ተግባር ነው፡፡ እንዲሁም አምልኮ ለእግዚአብሔር በመለየት እኛነታችን አሳልፈን በመስጠት ባረፈና በተዘጋጀ ልብ ሊፈጸም ይገባዋል፡፡ የግል አትኩሮታችንን ሁሉ ሰብሰብ በማድረግ አምልኮአችንን ማቅረብ ይጠበቅብናል፡፡ የምናመልከው አምላክ ክብር የተገባው ታላቁ አምላካችን ነውና፡፡ ስለዚህ በነቃና በማስተዋል መንፈስ እንድናመልክ ይጠበቅብናል፡፡

9) የክርስቲያን አምልኮ ገላጭና የሚቀርጽ ሊሆን ይገባል፡፡

አምልኮ ማህበረሰቡ የተለማመደውንና የሚያውቀውን እውነታ በታማኝነት የሚገልጥ ሊሆን ይገባል፡፡ በመዝሙረ ዳዊት እንደተገለጸው በነቃ መንፈስ በታማኝነት ዝማሬንና እምባን ምስጋናንና ንስሐን በመግለጥ የሚያሳይ ሊሆን ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አምልኮ የእኛ የራሳችን ቃል ያልሆነ ለምሳሌ እንደ "ጌታ ፀሎት" የመሳሰሉትን በማከል ከጌታ ጋር ባለን ግንኙነት እኛን በመቅረጽ ወደ አዲስ ጠለቅ ወዳለና ከእግዚአብሔር ጋር ሕይወት ወደምንካፈልበት ሊያዘልቀን የሚችል ሊሆን ይገባል፡፡

በዚህ ዓይነት ሁኔታ ስናመልክ የሚሰማው ቃል በመንፈስ የተመራ የደቀ መዝሙርነት ሕይወት መሣሪያ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ለጌታ ምስክር እንድንሆንና በባህሪው የተቀረጽን ታማኝ የጌታ ተከታዮች ያደርገናል፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የአምልኮ ደንቦች ምሳሌያዊ ናቸው እንጂ ፍፁማን መመሪያዎች አይደሉም፡፡ ይሁን እንጂ ለሁለት ሺህ ዓመታት የዘለቀውን የክርስቲያን አምልኮ ምንነት የሚያስረዱ ናቸው፡፡

በተጨማሪም እነዚህ መሠረታዊ ደንቦች በጣም አስፈላጊ ከመሆናቸው የተነሳ እንደ መጽሐፍት መግቢያነት ተቆጥረው ሊተዉ አይገባም፡፡ ይልቁንም በየሳምንቱ አምልኮ ለመምራት በሚዘጋጅ የአምልኮ መሪዎች ልቦና ልያቃጭሉ ይገባል እንጂ፡፡ በየሳምንቱ ለሚካሄደው አምልኮ ስርዓት ሃላፊ የሆኑ ሰዎች በሙሉ በደስታ ተልዕኮዎቻቸውን ለማሳካት አምልኳቸው በእውነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ እግዚአብሔርም ሰውም የሚናገርበት፣ ቃል ኪዳናዊ፤ ሥልሴን የማከለ ለሌሎች የሚራራ፣ ገላጭና የሚቀረጽ ግሩም የሆነ እንዲሆን ሊጥሩ ይገባል፡፡

በተጨማሪም እንዚህ ደንቦች በአንድነት እንዲገለጡ ልናስብበት የሚገባ ሥፍራ አለ፡፡ የክርስቲያን አምልኮ በአንድ ጊዜ ሥላሴን ያማከለና የሚራራ፣ ቃልኪዳናዊና በአለም ውስጥ ሆኖ ነገር ግን ከዓለም ያልሆነ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ትክክለኛ ምርጫ ማድረግ ይጠበቅብናል አልያም

የስነመለኮት እይታችንን ርህራሄ የሚጠይቀውን ዋጋ በመክፈል ማስፋት ወይም የስነመለኮት እይታችንን በርህራሄ ስም ማዳከም ሊሆን ይችላል፡፡

በዚህ ጽሁፍ የተገለጹት ጠቃሚ ሀሳቦች ለማህበረ ምዕመናን ምሳሌ እንዲሆኑ ታቅደው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ደንቦቹን የሚሰሩ መመሪያዎች አድርገን ስንወስዳቸው የትኛውም ልምምድ በአውዳችን መሰረት አምልኳችንን ከፍ ሊያደርግ እንደሚችል መረዳት እንዲኖረን ያግዛል፡፡ ልንጠይቀው የሚገባን ነገር ቢኖር በዚህ ጽሁፍ የተገለፁት ሀሳቦች በአጠቃላይ ከደንቦቹ የፈለቁና የማህበረ ምዕመናችንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሚዛን እንዲኖረው የሚያደርጉ ናቸውን? በግንኙነት ላይ የተመሰረተ ነው ወይ? እግዚአብሔርን የሚያስከብር ነው ወይ? ያንፃል ? የሚሉት ይሆናሉ፡፡

2. ለማምለክና አምልኮን ለመምራት መዘጋጀት፡-

ምናልባት እርሶ የአምልኮ ኮሚቴ ወይም የአምልኮ ዕቅድ አውጪ ቡድን ይሆናሉ ወይም ቤተክርስቲያናችሁ መጋቢ የላትም ይሆናል፡፡ ስለዚህ እርሶ የእሁድ አምልኮን በሚመለከቱ ጉዳዮች አንዳንድ ጉዳዮችን እንዲያዘጋጁ ተመርጠው ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም ደግሞ እርሶ መጋቢ ወይም የስነ-መለኮት ትምህርት ቤት ተማሪ ይሆናሉ፡፡ ምናልባትም አምልኮን በተመለከተ ያለዎትን ግንዛቤ ለማሳደግ ወይም ደግሞ የኮሌጅ ተማሪ ሆነው የተማሪዎች ህብረትን በአምልኮ ለመምራት ያቅዱ ይሆናል፡፡ ብቻ ምንም አይነት ሰው ይሁኑ ይህ መፅሃፍ አምልኮን ለመምራት በሚያደርጉት ዝግጅት አጋዥ ይሆኖታል፡፡

እርግጥ ነው ይህ መፅሐፍ ማይዳስሳቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ነገር ብቻ ብናነሳ የአምልኮ መሪ የሆነ ሰው ሊያሟላቸው የሚገቡ ወሳኝ የሆኑ ነገሮች ምን እንደሆኑ አያካትትም፡፡ የእግዚአብሔርን

ፍቅር የተሞላ፣ በመንፈስ በመነዳት የሚያመልክ፣ የመፅሐፍ ቅዱስ ዕውቀት ያለው መሆንን፣ ለምዕመኑና ማህበረሰቡ ፍቅር ያለው መሆን እንዳለበት ጠቅሶ አይተነትንም።

ሌላ ምሳሌ ደግሞ ብንጨምር ይህ መጽሐፍ የእያንዳንዱ ማህበረ ምዕመን የአምልኮ እቅድ ስለማውጠጥ ሂደትም አይዳስስም። ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ብዙ አጥቢያ ቤተ-ክርስቲያናት አሉና ። ሆኖም የዚህን መጽሐፍ ጠቃሚነት ለማጉላት የአምልኮ መሪና የአምልኮ እቅድ አውጪዎች ሚና ምን ሊሆን እንደሚገባ ማካተት አስፈላጊ ሆኖ አግኝነተዋል። ይህ መጽሐፍ ልንጠቀምበትና ደግሞም የራሳችን ልናደርገው የምንችለው ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያዎች ይሰጠናል። ቁልፍ የሆኑ መሠረታዊ የአምልኮ ዋና ሐሳቦችን ያነሳልናል። በተጨማሪም አምልኮን በተመለከተ አዳዲስ አቀራረቦችን በመዳሰስ ያስተዋውቀናል።

## 3.1. የአምልኮ እቅድ አውጪ እንደ ካህንና ነብይ፡-

እንደአምልኮ እቅድ አውጪነታችን በጣም አስፈላጊ ደግሞም አስፈሪ ተግባር እንፈጽማለን ይህ በሕዝቡ አንደበት ላይ በፀሎት የሚገለጡና በሌላም መልኩ የሚገለጡ ቃሎችን እናኖራለንና።እንደ አምልኮ እቅድ አውጪነታችን ደግሞም ካህናት ነንና የእግዚአብሔርን ህዝብ ፀሎት እንቀርፃለን። ልክ የብሉይ ኪዳን ካህናት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይወክሉ እንደነበር እንደዚሁም በዚህ ዘመንም የእግዚአብሔር ሕዝብ ፀሎት ቅርጽ እናሲዛለን።

እኛ ቅዱስ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል የማገልገል ሃላፊነት ተቀብለናል። የእለቱን የእግዚአብሔርን ቃል ስንመረጥና የምንመርጠውም ዋና ሀሳብ በእግዚአብሔር ሕዝብ መንፈሳዊ አመጋገብ ላይ ደግሞም

የሕይወት እንጀራን እንዴት እንደሚመገቡ በእግዚአብሔር ቃል ላይ **መጽሐፍ ቅዱሳዊ** ሚዛን እንዲኖረው የሚያደርጉ ናቸውን? በግንኙነት ላይ የተመሠረተ ነው ወይ? እግዚአብሔርን የሚያከብር ነው? የሚያንጽ ነው? የሚሉት ጥያቄዎች መጠየቅ ተገቢ ይሆናል፡፡

## 3.2. የአምልኮ ዕቅድ አውጪነት መልካም ባህሪያት፡-

የተዋጣለት የአምልኮ እቅድ አውጪ የሚያደርገን ምንድነው? በዚህ አገልግሎት ውጤታማ የካህንነትና የነብይነት ሚና እንዲኖረን ምን ያስፈልገናል? ሥራውን ለመፈጸም ፈቃደኝት ያስፈልገን ይሆን? ትልቅ መጽሐፍ ቤት ያስፈልግ ይሆን? ሥራውን ለመፈፀም ፈቃደኝነት ያስፈልግ ይሆን? እነዚህ መመሪያዎች የሚያስፈልጉ ቢሆንም ቅሉ፣ ለክህነትና ለነብይነት አገልግሎት ሚና በጥልቀት የሚጠቅመን አይመስለኝም፡፡

እስኪ የሚከተሉትን መልካም ባህሪዎች ደግሞ እንመልከት፡-

- ከአምልኮው ማህበረ ምዕመኑ የሚፈልገውንና የሚያስፈልገውን ርህራሄ አገልግሎት ማድረስ የሚችል፡፡
- ማን ነው አምልኮን ለመምራት ፀጋ ያለውና በምን ምልኩ ነው የሚመራው የሚለውን የመለየት ብቃት ያለው፡፡
- ከአምልኮ እቅድ አውጪ ቡድን ጋርና ከአምልኮ አመራር ሰጪ አካል ጋር በመተባበር የመስራት ችሎታ ያለው፡፡
- ማህበረ ምዕመኑ ለመስማት የሚችለውን ቃል ለማቅረብ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ያለውና የአምልኮ ማህበረሰቡን በሚገባ የሚረዳና የመጋቢነትን አገልግሎት መስጠት የሚችል፡፡
- በአምልኮ ሂደት በሕዝቡ ውስጥ ሊፈጠር የሚችለውን ስነመለኮታዊና ስነ-ልቦናዊ ግጭቶች መረዳት የሚችል ጥበብ ያለው፡፡

- ቃሉን ለማቅረብ መዝሙሮችን ለማዘጋጀት ፀጋና ፍላጎት ያለው እንደ አምልኮ አቅድ አውጪነታችን የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልና ዋና ሐሳብ ለእለቱ አምልኮ ማዕከል እንዲሆን ስንወስን ሁሉ የነብይት ሚና እንጫወታለን ማለት ነው። የብሉይ ኪዳን ነብያት የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝብ ያደርሱ እንደነበር በዚህ ዘመንም በፅሁፍ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ቃል ማህበረ ምዕመን የሚሰማበት መንገድ እንቀርፃለን።

ስለዚህ የአምልኮ አቅድ አውጪዎች የክህነትና የነብይነት ሚና ይጫወታሉ ማለት ነው። ቤተክርስቲያንና ማህበረ ምዕመናን ለእነዚህ ሚናዎች ዋና መንገድ ሊሆኑ ይገባል። ምክንያቱም አምልኮዎችንና እኛ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ምላሽ አግባብነት ያለው እንዲሆን የሚቀርጹ ናቸውና፣ የሥነ መለኮት ምሁራን የተማሩ ክርስቲያኖችን ስነ-መለኮት ግንዛቤ የሚቀርጹ መጽሐፍትን እንደሚጽፉ ሁሉ የአምልኮ አቅድ አውጪዎችም ደግሞ የእግዚአብሔርን ህዝብ የአምልኮ አገልግሎት ስነ-መለኮት የሚቀርጽ ሥራ ይሰራሉ።

በዚህ ምክንያት የአምልኮ አቅድ አውጪነት የኛ ነው። አትኩሮትን የሚስብ፣ ጥረት የሚጠይቅና የሚማርክ ሃላፊነት ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ የአምልኮ አቅድ አውጪዎች የአምልኮ አቅድ አውጪነትን የአጭር ጊዜ የስልክ ንግግር አድርገው በመቁጠር ትልቅ ስህተት ይፈጽማሉ። ምናልባት አንዳንድ ጊዜ አጭር ዝግጅት እንደየአውዱ ጥሩ አቅድ ሊሆን ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ እንደዚህ ዓይነት አቅድ በትክክለኛ አምልኮ ፍትሐዊነቱ አጠራጣሪ ነው። መጠየቅ ያለበት *"እንዴት በፍጥነት እንዳቀድነው ሳይሆን መሆን ያለበት "እንዴት ነው ይህ አገልግሎት በታማኝነትና በልዩ ሁኔታ ሕይወት የሚሰጠው"* የሚለው ሊሆን ይገባል።

- ከልክ በላይ ወይም ያለፈ ፈጠራን ወይም እንዲው የወረደ አቀራረብ ይዞ እንዳይቀርብ በነገር ሁሉ ራሱን የሚገዛ መሆን አለበት። ምክንያም የአምልኮ አቅድ መንደፍ ማለት የስነጥበብ ወይም የስነ ግጥም ዘዴ መጠቀም ማለት አይደለም። እኛ የምናቅደው ለአምልኮ የሚሰበሰብን ማህበረሰብ የሚደርስ መንፈሳዊ ተግባር ነው። ከልክ ያለፈ ስነጥበብ ስንጠቀም ማህበረሰቡ ተቋቁሞ ላይዘልቅ ይችላል። ምክንያቱም የትኛውም ማህበረ ምዕመን ፈጠራ በሆነ ቅንብር መፀለይና ከልቡ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እጅግ ያዳግተዋልና። በሌላ መልኩ ደግሞ በጣም የወረደ የአምልኮ አቀራረብ ጉባኤውን ያደክመውና ምላሽ የማይሰጥ ጉባኤ እንዲሆን ያደርገዋል።

እንግዲህ እነዚህ የተጠቀሱት የአምልኮ እቅድ አውጪ ባህሪያት ላይ ትኩረት አድርገው የሚያቅዱ ናቸው አምልኮን ትልቅና ትርጉም የሚሰጥ የሚያደርጉት።

ምናልባትም እነዚህ ዝርዝሮች ያልተሟሉ ሊመለስለን ይችል ይሆናል። ማስታወስ ያለብን ግን ማናችንም ብንሆን በተፈጥሮ ሁሉንም መልካም ባህሪያት የሌለን መሆኑ ነው። እንደዚሁም ደግሞ ማንም ሰው ሁልጊዜ በእነዚህ ባህሪያት መኖር አይችልም። የአዲስ ኪዳን መልካም ዜና እንደሚያበስረን እነዚህን መልካም ባህሪያት ለመላበስ መጣር ብቻ ሳይሆን አማኙን ማህበረሰብ ለማነጽ የመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ሥጦታ መሆናቸውንም ማወቅ ጭምርም ነው።

እንደ አምልኮ እቅድ አውጪነታችን መጀመሪያ ልናደርገው የሚገባ ነገር ቢኖር በፀሎት እነዚህ ስጦታዎች በሕይወታችን እንዲገለጡ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ነው። የትኛውም የጎደለ መልካም አሰራር ቢኖር ወደ ማህበረ ምዕመኑ በመመልከት ያንን ፀጋ ያለውን ሰው በመፈለግ ፀጋውን እንዲያካፍል መጋበዝ ነው።

የአምልኮ እቅድ ማዘጋጀት አምልኮን መምራትና መገምገም ብዙዎችን በጥልቀት የሚያሳትፍ ነው፡፡ አምልኮን ለማቀድ የምንጠቀምባቸው መጽሐፍት፣ የመዝሙር ደብተሮችና ሌሎች ምንጮች ጥቅማቸው አነስተኛ ቢመስልም ነገር ግን በጣም አስፈላጊ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡ በእውነተኛ የክህነት አገልግሎት የሚሰጥ ፀሎት ከእውነተኛ የፀሎት ሕይወት የሚገኝ ነው፡፡ ሆኖም አንዳንዴ ደግሞ ይህም ቢሆን የአምልኮ ጉባኤዎችን በሞላ ወደ ፀሎት ውስጥ እንዲገባ ላይረዳን ይችል ይሆናል፡፡ ስለዚህ ደግሞ በተለይም ከመጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ቦታና ጊዜ ከተደረጉ የአምልኮ ጉባኤዎች የምንቀስመው መልካም ነገር ይኖራል፡፡

ለዚህም በተለያየ ቦታ የተዘመሩ መዝሙራት፣ የመዝሙር መጽሐፍትንና ስብስብ የፀሎት መጽሐፍቶች መጠቀም ያስፈልገናል፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ማህበረ ምዕመን የሚጠቀምበት መዝሙሮችና የመዝሙር መጽሐፍት ማዘጋጀት ቢቻል መልካም ነው፡፡ አንዳንዴም ለመጠቀም የምናዘጋጃቸው መዝሙሮች ከደራሲው ድምጽ ቅላጼ ወይም የሙዚቃ አጠቃቀም ሊለይ ይችል ይሆናል፡፡

ስለዚህ ነው መጽሐፍት ሲዘጋጁ በትክክለኛ ቅላጼው ማዘጋጀት የሚያስፈልገን፡፡ እነዚህ የሚዘጋጁ መጽሐፍት በተለያየ ጊዜና ቦታ የተከናወኑ የአምልኮ ጥበቦችን ያስተምሩናል፡፡ እያንዳንዳችን በግል ከምናደርገው አምልኮ ይልቅ ሰፋ ባለ እይታ አምልኮዎችንና ምስጋናችንን እንድንሰዋ ያግዙናል፡፡ ዝማሬው በሙዚቃ ታጅቦ ሲቀርብ የዝማሬው ቃል ልክ የራሳችን እንደሆነ አድርገን እንዘምረዋለን፡፡ ስንዘምር የራሳችንን ድምጽ ቅላጼ በመጠቀም የምንዘምረው ቃል ዋጋ ያለው እንዲሆን እናደርጋለን፡፡

ለአምልኮ እቅድ አውጪነት የሚያስፈልገን መልካም ባህሪያት ባይሆኑም እንኳን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ግብዓቶች የአምልኮ

እቅድ አውጪዎችና መሪዎች የክህነትና የነብይነት አገልግሎታቸውን በታማኝነት እንዲወጡ ይረዳሉ የሚል እምነት አለኝ።

በአንዳንድ ባህሎች የአምልኮ መሪዎች በጋለ ስሜት እንዲመሩ ይበረታታሉ። በሌላ ባህል ደግሞ ለስሜት ምንም ቦታ የማይሰጥበት ሁኔታ ያጋጥማል። በአንድንድ ባህል ደግሞ የአምልኮ መሪዎች በጽሁፍ የተዘጋጀ ፀሎት እንዲፀልዩ ይገደዳሉ። ሌላ ቦታ ደግሞ የአምልኮ መሪዎች ያለዝግጅት እንደመጣላቸው እንዲፀልዩ ይፈቅድላቸዋል። ይህ መጽሐፍ ደግሞ እዚህን ሁሉ ባካተተ መልኩ እንዲያገለግል ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። ከአምልኮ መሪዎች የሚጠበቀው ዋና ነገር የትኛው ለየትኛው ዓይነት ክርስቲያን ማህበረሰብ ውጤታማ በሆነ መልኩ ሊጠቅም እንደሚችል ለይቶ ሥራ ላይ ማዋል መቻል ነው።

## 3.3. የአምልኮ ጊዜ ቃሎቻችን

በእርግጥ አምልኮ ከቃል በብዙ ያለፈ ነው። ይሁን እንጂ በአምልኮ ጊዜ በአብዛኛው ብዙ ቃላቶች ጥቅም ላይ ይውላሉ። በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ በፀጥታ ሆነን በማሰላሰል ወይም በሙዚቃ ቅንብር ብቻ ከቃሎች ወደ ሚበልጥ ተመስጦ ልንገባ እንችላለን። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን አምልኮ አብዛኛው በቃሎች ላይ የተመረኮዘ ነው።

ስለድነት ጉዳይ ቢሆን ስለራሳችንና ስለእግዚአብሔር ልናውቀውና ልንናገረው የሚገባን ግንዛቤ ሁሉ እንኳ ቢሆን በፍጥረታት ብቻ አልተገለጠም ነገር ግን በእግዚአብሔርም ቃል ጭምር ነው እንጂ። የሕብረት አምልኳችን እንኳ በራሱ ውጤታማ የሚሆነው እርስ በራሳችን መነጋገር ስንችል፣ እንድናመልክ ስንሰበሰብ፣ ለእርስ በእርሳችን የጋራ ፀሎቶች ተከፋፍለን ስንፀልይና አንዳችን ለአንዳችን በእምነታችን እንድናድግ ስንበረታታ ነው።

ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ በሙዚቃ የምንሳበውን ያህል እንኳ ለእርስ በርሳችን በቃል መነጋገር ብዙም ትኩረት አንሰጠውም። ልብ ብንል በየዓመቱ እርስ በርስ ለመነጋገር የምንሰጠው ጊዜ በአብዛኛው ያነሰ ነው። በእርስ በርሳችን መካከል የሚደረግ መነጋገር እንደ እግዚአብሔር ስጦታ ቆጥረን ልንጠቀምበት ይገባል። የአምልኮ ሥርዓት በራሱ መልካም ባህሪይ አይደለም። ነገር ግን የበለጠ ዋጋ ሊሰጠው የሚገባ ነገር ቢኖር በእርስ በእርሳችን መካከል ለመበረታታት ሌላውን ደግሞ ለማዳመጥና በእርሱ ጉዳይ ተካፋይ በመሆን ወቅታዊ ፀሎት መፀለይን በመካከላችን እየጨመረ እንዲሄድ ማድረግ ይገባል።

አብዛኛውን ጊዜ ተግዳሮት የሚሆንብን ጉዳይ ቢኖር በአምልኮ ጊዜ የሚዋጠው የሁሉንም ሰዎች አምልኮትና ፀሎት በሚገለጠው በጥቂት ሰዎች ቃሎች መሆኑን ነው። በሚያመልኩ ሰዎች እይታ ሁልጊዜ የአምልኮ ቃሎች ከጥቂት ሰዎች በኩል የሚቀርብ ነው። የአምልኮት አቅራቢያዎች ሁልጊዜ አንዱ ሰው በሚያቀርበው ቃል እናመልካለን። ይህንንም ቃል ደግሞ የመማር ፈጣን ግንዛቤ ደግሞ አለን። ይህን ግንዛቤ ደግሞ ለየት ያለ የሰው ልጅ የግንዛቤ ችሎታ ያዘለ ነው። ማህበረሰቡ የሰጠንን ቃል ተቀብለን በእምነት እንሄዳለን ቃሉ እንኳ በትክክል ባይቀርብ ጥርጣሬን ታግሰን በፀጋ እንወጣለን፤ የሰማነውን ከራሳችን ጋር የማዋሃዱ መሻት ደግሞ አለን።

በእርግጥ የአምልኮ አገልግሎት እውነታ እያንዳንዱ የማህበሩ አምልኮት አቅራቢ በነቃ መንፈስ ከልብ በአእምሮ በነፍስ በፈቃድና በሰውነትም ለተነገሩት መልካም ቃሎች ሁሉ በመስጠት የተሰፋ እንደሆነ ነው። ሆኖም መዝሙር የዘመረ ሁሉ ከልብ በአእምሮና በፈቃድ በሁሉ ተሳትፎአል ሊያስብል ይችላል። የመመሰጥ መጠን ምናልበትም አንዳንዴ በሰውነት እንቅስቃሴ ሊገለጥ ይችላል። ይህም ቢሆን በቂ ሳይሆን

ይችላል፡፡ ምንም እንቅስቃሴ ያላሳየ ሰው ደግሞ ምናልባት በውስጡ በጣም ተነሳስቶ ሊሆን ይችላል፡፡

ምናልባት አንዳንዶች በጣም የሚንቀሳቀሱት የሙዚቃ ውበት ስቧቸው የቃሉ አገላለጽ አድናቂ ሆነው እንጂ በአምልኮ ተነክተው ላይሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ልክ እንደ ሙዚቃ ውበትም የአምልኮ ቋንቋ ግብም ማህበሩ እግዚአብሔርን እንዲያመልክ የማሰብ የሚያነሳሳ ሊሆን ይገባል፡፡ በእርግጥ ይህ ግብ አብዛኛውን ጊዜ አይጨበጥም፡፡ ይሁን እንጂ ምሳሌ የሚሆኑትንም በመመልከት በጊዜ ሂደትም ቢሆን አምልኮዎችን በሚገባ ቃል መቅረጽ የተገባ ነው፡፡ በአምልኮ ወቅት ስለምንጠቀምባቸው ቃላት በተመለከተ የሚከተሉትን ሦስት ግቦችና መስፈርቶች መመልከት ይጠቅማል፡፡

1) ቃላችን ለክርስቶስ ወንጌልና ለመጽሐፍ ቅዱስ ታማኝ የሆነ መሆን አለበት፡፡

የዚህ ክፍል ግብ የተመጣጠነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዋና ዋና ሀሳቦችን መዳሰስ ይሆናል፡፡ ስለ እግዚአብሔር ስንናገር አምላካችን ታላቅ ንጉስ ሩህሩህ ደግሞም አጽናኝና ጌታ መሆኑ ይገባናል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም በክርስቶስ ድነት ፍፁም የማዳን ሥራ ወደ ፍጥረት ሁሉ የዘለቀና ባህልን ሁሉ ተሸጋሪ መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ ስለቤተክርስቲያን ደግሞ ስንናገር ልገልጸው የሚገባ ነገር ቢኖር የአማኞች ማህበር መሆኑን፤ ደግሞ ቸርነት አድራጊና እውነትን የምትገልጥ፤ የክርስቶስን ወንጌል የምታበስረኝ በምድር ላይ ሰላምና ፍትህ እንዲሰፍን የምትሰራ መሆኑዋን ሊሆን ይገባል፡፡

በተለይም በኛ ዘመን ስለእግዚአብሔር የምንናገረበት ቋንቋ ቀጣይነት ያለው ሲሆን ይገባል፡፡ በተለይም የእግዚአብሔርን ስሞች፣ ስዕላዊ አገላለጦችና በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የተገለጡትን የእግዚአብሔርን ማንነቶች የሚገልጹ ሀሳቦችን በመጠቀም ልንገልጠው

ይገባል፡፡ ምናልባትም ይህ አባባል ሁሉንም ላያረካ ይችል ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚነሱ ውዝግቦችን ማርገብ ይቻላል፡፡

2) ማህበረ ምዕመኑ ሊረዳውና ሊገነዘበው በሚችለው ቃላት መጠቀም ያስፈልጋል

በአምልኮ ወቅት የሚገለጡ ቃላቶች የከበሩና ሕዝቡ በቀላሉ ሊያገኘው የሚችል ሊረዳው የሚችለው እንደዚሁም በሕሊናው ተቀርፆ የሚቀር ቢሆን እጅግ ይመረጣል፡፡ በአምልኮ የምንናነገረው ቃል ሁሉንም የማህበረ ምዕመኑ አካል የሆነ ማለትም ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ አዲስ ክርስቲያኖች፤ ረጅም ዘመን የቆዩ አማኞችን ሁሉ የሚያካትት ሊሆን ያስፈልጋል፡፡

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በእርግጥም ማህበረ ምዕመኑ በአምልኮ በሚገባ እንዲሳተፍ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንደዚሁም አምልኮት አቅራቢዎች በሕብረት ፀሎት እንዲሳተፉ ማነሳሳትም የቤተክርስቲያን *ሥራ* ነው፡፡ በእርግጥ ማህበሩ በጥልቀት እንዲካፈል ለማድረግ ጊዜ ይወስዳል ለምሳሌ ያህል አንዳንድ ጉባኤ በንስሐ ፀሎት ጊዜ መንበርከክን ይመርጣል በዝማሬ ወቅት ደግሞ እጁን በማንሳት ማመስገን ይወድ ይሆናል ሌላው ጉባኤ ደግሞ የዕለቱ ቃል ከተነበበ በኋላ አንባቢው *"ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡"* ሲል ጉባኤው ደግሞ *"እግዚአብሔር ይመስገን"* በማለት በአንድነት የመመለስ ልማድ አለው ይሆናል፡፡

ሆኖም ግን እንዚህ ሁሉ በሁሉም ጉባኤ ወጥ በሆነ መልኩ እንዲለመድ ማድረግ ጊዜ ሊወስድ ይችላል፡፡ ነገር ግን ከብዙ ጥረት በኋላ ሊሳካና ሊጨበጥ የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ የሚያስፈልገን ሁለቱንም ማለት

ልምድ እንዳለን የሚያሳይና ወደ ጠለቀ ልምምድ የሚከተን የቃላት አጠቃቀምን ነው፡፡

በግልና በማህበር የሚገለጥ ጤነኛ የሆነ የፀሎት ሕይወት በሁለት ዓይነት ፀሎቶች ዙሪያ ያጠነጥናል፡፡ በመጀመሪያ አንዳንድ ፀላዮች ውስን ናቸው፡፡ በዝግጅት ላይ ያልተመሠረተ የግል እና ቅጽበታዊ ፀሎት ነው የሚፀልዩት፡፡ እንደዚህ ዓይነት ፀሎት የሚፀልዩ ሰዎች መነሻቸው ልምምዳቸው ነው፡፡ ለምሳሌ *"ጌታ እግዚአብሔር በዚህ በማይታመንና ፍርሃት ባለበት ጊዜ ማህበረ ምዕመናችንን እርዳ…"* ሁለተኛ አንዳንድ ፀላዮች የማህበር ፀሎት ላይ ያኮራሉ ወይም *"የተሰጠ"* እንዲያውም በጉባኤው ላይ *"ጫና የሚፈጥር"* ፀሎት ይፀልያሉ፡፡ እስቲ የጌታን ፀሎት ስለሚፀልዩ ልጆች ለአንድ አፍታ ያስቡ ምናልባትም ቃሉ ምን እንደሆነ ሳይገባቸው ፀሎቱን መፀለይ ይማሩታል በጊዜ ሂደት ግን ትርጉሙ ይረዱታል፡፡ በዚህም ሁኔታ ያድጋሉ በሕይወታቸውም ዘመን ሁሉ በመስጠት መፀለይን ይማራሉ፡፡ አስቲ አንድ አፍታ ደግሞ አንድ ወንጌላዊ አዲስ ሰው መፀለይ እንዲችል "ይህንን ፀሎት ከእኔ ጋር ፀልይ" ብሎ ሲያለማምድ ያስቡ ወይም ደግሞ ከመዝሙር ዳዊት መፀለይን ያስቡ፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምሳሌዎች የፀሎት ሕይወታችን በራሳችን ሀሳብ ልምምድና ስሜት ላይ ብቻ ባለመወሰኑ የታደልን ነን፡፡ ይልቁን ከራሳችን ወደ ሚበልጥ ወደ ትልቅ ነገር የሚጋብዘን ነው፡፡

በአምልኮ ጊዜ ስለሚገለጠውና በዚህ መጽሐፍ ደግሞ ስለተጻፈው ቃል የመጨረሻ ማሳሰቢያ ማለት የምፈልገው ነገር ቢኖር በሙዚቃ እንደሚገለጠው ያህል የመጽሐፍ ቃል ያን ያህል ጠቃሚ ላይሆን ይችላል፡፡ ውጤታማነቱ ግን ቃሉ ወደ ሕይወት በሚያመጣው ሰው ንግግር ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ አንድ ዓይነት ከተዘጋጀ መጽ ሐፍ ወይም ከመጣጥፍ ተመርኩዞ ማንበብ ሕይወት የማይሰጥ ወይም ሙት

የሆነ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ ቃሉ እንዴት ተደርጎ ጥቅም ላይ በማዋሉ ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ጉዳይ እውነት የሚሆነው ለልጆች ትክክለኛ ቃል ለማቅረብ በምናሰየው ጥረት ነው፡፡

ለአምልኮ የሚያበረታቱ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ልጆችን በሙሉ ኃይላቸው በአምልኮ እንዲሳተፉ ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህም በመልካም ሥራቸው ሊበረታቱ ይገባል፡፡ እንግዲህ ይህ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ የአምልኳችን ቋንቋ ልጃችንም ያካተተና ሊደረስበት የሚችል ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ለልጆች የሚነገር ቃል ዝቅ ያለ ወይም በጣም የተለየ ይሁን ማለታችን አይደለም፡፡ ቃሉ ትክክል ከሆነ በድምጽ ቅላጽያችን እንኳ ለእነርሱ ትርጉም እንዲሰጥ ማድረግ እንችላለንና አብዛኛውን ጊዜ መሪዎች ለልጆች ሲናገሩ የልጅ ንግግር ሳይሆን የሚፈልጉት ልጆችን የሚመጥን ንግግር ነው፡፡ ለልጆች በጣም ሳይቃለል መናገር ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም ነው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ *"ልጆችን የሚመጥን"* ጽሁፍ የተካተተው ቃሉ በራሱ በቂ አይደለም ነገር ግን በአክብሮት ለልጆች እንደሚሆን የሚናገረው ሰው ያስፈልጋልና፡፡

## 3.4. የአምልኮ ሥርዓት፡- ከክርስቲያናአዊ ልምምድ ጥበብን መማር

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ ነው የሚባል አንድ ወጥ የሆነ የአምልኮ ሥነ-ሥርዓት ተጽፎ አናገኝም የሆነ ዓይነት የአምልኮ ሥነ ስርዓት እንኳ ቢኖር ፍጹም ትክክል ነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ታማኝና ሕይወት ያለው ነው ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡ የአምልኮ ስነ ስርዓትን አስመልክቶ ሊጤን የሚገባው ነገር ቢኖር ውጤታማ የምንለው የአምልኮ ሥርዓት በጥንቃቄ የተዘጋጀና በታማኝነት ደግሞ *"ከላይ በተገለፀው"* መሠረት ተግባራዊ የሚደረግ ከሆነ ነው፡፡ ወጥ በሆነ ሁኔታ የተለመደ

የአምልኮ ሥርዓት የተመጣጠነ መንፈሳዊ ማዕድ ለማህበሩ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

በተጨማሪም ወጥ የሆነ የአምልኮ ሥርዓት አንዳንድ የሚነቃቁና በፈጠራ የተካኑ የአምልኮ መሪዎች የራሳቸውን አጀንዳ ብቻ እንዳያስተናግዱ ያግዳቸዋል፡፡ ከፊት ያለውን እየጠቆመ አምልኮን የሚያስኬድ ሥነ-ስርዓት ማህበር ምዕመኑ ልቡ ተነስቶ እንዲጠባበቅ ከማድረጉም በላይ አንዳንዶቻችና ልጆቻቸውም ጭምር ሁልጊዜ የጉባኤዎችን አዘውትሮዎች እንደሆኑ ያነሳሳቸዋል፡፡

በጣም አስፈላጊ ነገር ቢኖር በትክክል የተቀረፀ የአምልኮ ስነ-ስርዓት የአምልኮውን ዋና አላማ በሥራ ላይ እንደሚውል ያስረግጣል፡፡ በሌላ አባባል በጽኑ ታስቦ የተዘጋጀ የአምልኮ ሥነ-ስርዓት አምልኮ አምልኮነቱን የጠበቀ እንዲሆን ያግዛል፡፡ እንደዚሁም ደግሞ የአምልኮ ሥርዓት አምልኮን የመምራት መለማመጃ ጊዜ ከማድረግ እንደ መዝናኛ በመቁጠርና የአንዳንዶች ችሎታ ማሳያ ጊዜ ከመሆን ይከላከላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በአንዳንዶች ዘንድ የአምልኮ ስርዓት የሚያፍን ጉባኤን የሚያስርና የፈጠራ ችሎታን የሚቀንስ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ እስቲ የጃዝ ሙዚቃን ልብ በሉ፡፡ ጃዝ ያለምንም ዝግጅት ከውስጥ የሆነ የሙዚቃ እንቅስቃሴን ያፈልቃል፡፡ ይሁን እንጂ ጃዝ ተጫዋቹ በያቋርጥና ቀጥሎ ያለውን በሚጠቁም መልኩ የተደጋገመ የቅኝት አወቃቀር ላይ አትኩሮ በመጫወቱ ነው፡፡ ያለ ቅኝት ሲዋቀር ሙዚቃው ቀውስ ፈጣሪ ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህ ትርጉም የሚሰጥ ሙዚቃ እንዲሆን ከተፈለገ በሥርዓቱ ተጠንቶ በተዋቀረ ዘዴ መጫወት ያስፈልጋል፡፡

እንደዚሁም ደግሞ ልብ ብለን ከሆነ የአምልኮ ሥርዓቱ በጽሁፍ ይገለጥ ወይም አይገለጽ እያንዳንዱ ማህበረ ምዕመን ቀጥሎ የሚሆነውን

በሚጠቁም ዓይነት ሥርዓት የዋቀረ ነው፡፡ አንዳንድ ማህበረ ምዕመናን በጽሁፍ የተዘጋጀ የአምልኮ ሥርዓትንና ወጥ የሆነ ልምምድን ይቃወማሉ፡፡ ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ ሥርዓት ቀጥሎ የሚሆነውን የሚጠቁም ጠቋሚ ነገር ነው፡፡ የአምልኮ ሥርዓቱ ታትሞ ባይወጣም እንኳ ጥሩ የአምልኮ እቅድ አውጪዎችና የአምልኮ መሪዎች የማህበረ ምዕመናናቸውን የአምልኮ ስርዓት በመረዳት አምልኮውን ውጤታ እንደሆነ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

በሁለቱም ማለትም በአምልኮ ሥርዓት አወቃቀርና በአምልኮ ዓይነት ግራ መጋባት አስፈላጊ አይደለም፡፡ በሌጎስ ናይጀሪያ እና በካንሳስ ከፊል ገጠራማና ከፊል ከተማ በሆነ አካባቢ በሚደረግ የአምልኮ ዓይነት በአመራር ልዩነትና በሙዚቃው ባህል ሊለያይ ይችላል፡፡ ነገር ግን ከስነመለኮት አስተምህሮ አንጻር ደግሞ ስንለመከት አንድ ዓይነት አወቃቀር ሊኖራቸው ይችላል፡፡

# ምዕራፍ አራት

*"መልስ የሌለው አምልኮ የለምና የሚሰማ ጩኸት ጩኸህ መልስህን ተቀበል"።*

# የአምልኮ መገለጫዎች

**ዓላማው፡- መጽሐፍ ቅዱሳዊ የአምልኮ መገለጫዎችን ለይተን ለመገንዘብና እውቀት በሌለው መልክ ሳይሆን መስጠትና በመገዛት ማምለክ እንድንችል ነው።**

## 4.1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዳሰሳ፡-

ከብሉይ ኪዳን እስከ አዲስ ኪዳን ድረስ ብንዳስስ አምልኮ እግዚአብሔርን በመባረክ፤ እርሱንም በማወደስ፤ በፊቱ በመንበርከክና በመስገድ፤ በመዘርጋትም ሆነ ለጥ ብሎ እጅ በመነሳት፣ ሀሴት በማድረግና በደስታ በመዝለል የሚገለጽ ለእግዚአብሔር ውለታ ምላሽ የመስጠት ተግባር ነው። ይህም ከብዙ በጥቂቱ በሚከተለው ሁኔታ ይገለጻል።

### ሀ) በብሉይ ኪዳን

እግዚአብሔር ለባህሪውና ለክብሩ መግለጫነት የፈጠረው ክቡር ሰው በኃጢአት ምክንያት ከአምላኩ ቢለይም ከእግዚአብሔር ቸርነትና ለሰዎችም ካዘጋጀው የማዳን መንገድና ተስፋ የተነሳ የሰው ልጅ መስዋዕትን በማቅረብ እግዚአብሔርን ማምለክ ጀመረ/ ዘፍ 3፡15-21, 4፡2-4, 8፡20-21/

እንዲሁም በአብርሃም ዘመን አምልኮ መሰዊያን ከመሥራት መስዋዕትን ከማቅረብ እና የእግዚአብሔርን ስም ከመጥራት ጋር የሚፈፀም ከመሆኑም በተጨማሪ በተወሰኑ ሥፍራዎች የሚፈጸም ነበር። እነዚህም

ስፍራዎች እግዚአብሔር እራሱን የገለጠባቸው ስፍራዎች ናቸው። ዘፍ12፡7-8, 13፡4, 18፡21፡33

በእነዚህ ስፍራዎች የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኘት አይነተኛው የአምልኮ ተግባር ነበር። አባቶች በእነዚህ የተወሰኑ ስፍራዎች ላይ ያኮራቸው ዋናው ምክንያት በተጠቀሱት ሥፍራዎች እግዚአብሔር እራሱን መግለጡ ነበር። ቤተ መቅደሱም በኢየሩሳሌም እስከተሰራበት ዘመን ድረስ የነበሩ የአምልኮ ስፍራዎች ጌልጌላ ወይም የስሙ ትርጉም መንከባለል ማለት ነው። ኢያሱ 5፡7-12, 18፡1-10 ምጽጳ መሣ 20፡1-8 ገባኦን፣ 1ኛ ዜና 16፡39፡21፡29፤ ኦፍራ, መሣ 6፡22-24, ዳን , መሣ 17፡18 ናቸው።

ሌላው በብሉይ ኪዳን የምንለከተው የአምልኮ መግለጫ ስግደት ነው። ዘፍ 22፡5, 24፡26, 48, 52 ስግደት ሰው ለፈጣሪው ለአምላኩ ያለውን ተገዥነትና ታዛዥነት የሚገልጽበት የአምልኮ ተግባር ሲሆን ከምስጋና እና ከዝማሬ ጋር ተጣምሮ ሊቀርብ ይችላል። ዘፍ24፡48, 2ኛ ዜና 7፡3-4, 29-30

- ✓ በአባቶች ታሪክ አምልኮ ውስጥ እግዚአብሔርን መባረክና ማክበር /ማመስገን/ እንደ አንድ የአምልኮ መግለጫነት ተገልጾ እናያለን። ዘፍ 9፡26, 14፡20, 24፡27, 29፡35
- ✓ ወደ ዘፀዓት መጽሐፍ ስንመጣ እግዚአብሔር ህዝቡን ከግብጽ ምድር የማውጣት ዋና ዓላማው ከግብጽዉያን ባርነት ህዝቡን ተቤዥቶ እርሱን የሚያመልክ የሚያገለግል ህዝብ ለራሱ ማድረግ እንደሆነ እንመለከታለን። ዘፀ 2፡12-18, 10፡25
- ✓ ይህ ጥቅስ ለአገልጋዮችና ህዝቡም ጭምር የአባቶቻቸውን አምላክ ለማምለክ መጠራታቸው ግልጽ እንዲሆንላቸው ያመለክታል።

- ✓ ሕዝቡም ከግብጽ ምድር በወጡ ጊዜ በዝማሬ የአምላካቸውን ታላቅነትና ያደረገላቸውን ማዳን በማድነቅ አመለኩት፡፡ ዘፀ (15) ከዚህም በተጨማሪም ህዝቡ እግዚአብሔር በሰጣቸው መሪ በሙሴ በኩል እግዚአብሐር የሚናገራቸውን ቃል/ትዕዛዝ/ ከመስማትና ለታዘዙትም ቃል ተገቢ ምላሽ በመስጠጥ /በመታዘዝ/ ጭምር እግዚአብሐርን ያመልኩት ነበር፡፡ ዘፀ 24፡1-18
- ✓ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ለመገናኛው ድንኳንና ለቤተመቅደሱ ሥራ ሥጦታን /መባን/ በመስጠትና/ ዘፀ 25፡1, ዘኁ35፡50, 2ሣሙ 8፡11, 1ዜና 246-9, ዕዝ 8፡28, ምሣ 3፡9 እንዲሁም ለእግዚአብሔር ስለታቸውንና ለመስዋዕት የሚሆኑ እንስሳትን በማቅረብ እግዚአብሔርን ያመልኩት እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ ዘኁ 15፡3, 28፡1-2, ዘዳ 12፡5-6, ዕዝ3፡5,7፡16-17
- ✓ ከግብጽ ከመውጣታቸው ጀምሮ እግዚአብሔር በሰጣቸው በዓላት /በፋሲካ፣ በሰንበት፣ በበዓል ሀምሳ፣ በአዲስ ዓመት መባቻ፣ በዳስ በዓል፣ በሰባተኛው ዓመትና በኢዮቤልዩ ዓመት እንዲሁም በዕለታዊ የአምልኮ ስርዓት/ የእግዚአብሔርን ማዳን፣ በጎነቱን፣ ቸርነቱን፣ ባርኮቱን በማሰብና ሥጦታንና መስዋዕትን በማቅረብና ትዕዛዙን በመጠበቅና በመፈጸም እግዚአብሔርን ያመልኩት ነበር፡፡ ዘፀ 29፡18, ዘኁ 28፡3, 2ኛ ሳሙ 24፡25, 1ነገ 3፡4, 1ኛ ዜና 16፡40-43
- ✓ ሌላው የብሉይ ኪዳን አምልኮ ሲነሳ ሳንመለከተው የማናልፈው ነገር እግዚአብሔርን ለማምለክ ቅድስና መሟላት ያለበት ዋነኛ

ተቀዳሚ ሁኔታ መሆኑን ነው/ ዘፀ 12፡10-15, 2ተኛ ሳሙ 12፡20, ዘኁ 8፡1/

✓ በ586-587 ዓ.ዓ ኢየሩሳሌም በጠላት ተወራ ቤተመቅደሱ ፈርሶ ህዝቡም ወደ ባቢሎን በምርኮ ተወስዶ በዚያም ለ70 ዓመታት ቆይተዋል፡፡ በጊዜውም የመስዋዕት አምልኮ የተቋረጠ ቢሆንም እንኳ በተቻላቸው መንገድ በምኩራቦች በመሰባሰብ ይህንን መጽሐፍ በማንበብና ለሰሙትም ቃል ምላሽን በመስጠት /በመታዘዝ/ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር፡፡

ከብሉይ ኪዳን የአምልኮ መገለጫዎች

✧ መባረክ፡- መዝ 34፡1, 1ዜና 29፡20

እግዚአብሔርን ሁሉ ጊዜ እባርከዋለሁ ምስጋናውም ዘወትር በአፌ ነው፡፡

"ዳዊትም ጉባኤውን ሁሉ አምላካችሁን እግዚአሔርን ባርኩ አላቸው፡፡ ጉባኤውም ሁሉ የአባታቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ባርኩ፤ ራሳቸውንም አዘንብለው ለእግዚአብሔርና ለንጉሱ ሰገዱ፡፡"

✧ ማወደስ፡- መዝ 22፡23, 61፡8

እግዚአብሔርን የምትፈሩት አመስግኑት ያዕቆብ ዘር ሁላችሁ የእስራኤልም ዘር ሁላችሁ ፍሩት፡፡

✧ መንበርከክ፡- መዝ 29፡1

የስሙን ክብር ለእግዚአብሔር አምጡ፤ በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ፡፡

✧ መዘመር፡- መዝ 66፡2

ለስሙም ዘምሩ ለምስጋናውም ክብርን ስጡ፡፡

✧ መስገድ /ለጥ ብሎ እጅ መንሳት/፡- ዘፍ 24፡26, ዘፀ 4፡31, ኢያ 5፡13-15

(… ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደና ጌታም ለባሪያው የሚነግረው ምንድር ነው? አለው። የእግዚአብሔርም ሠራዊት አለቃ ኢያሱን አንተ የቆመህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው። ኢያሱም እንዲሁ አደረገ።) ኢያሱ 5፡13-15

ለ) በአዲስ ኪዳን፡-

"የአዲስ ኪዳን የአምልኮ ማዕከል ክርስቶስ ነው" በዮሐንስ ወንጌል 4፡20፡24 ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ያደረገው ውይይት የአዲስ ኪዳን አምልኮ ቅርጽና ይዘት ሊያመለክት የቻለበትን ነጥቦች ከዚህ በታች እንመለከታለን።

1) በብሉይ ኪዳን በተወሰኑ ስፍራዎች ብቻ ለእግዚአብሔር ይቀርብ የነበረው የአምልኮ ሥርዓት በዚያ መልክ ሊቀጥል የማይችልበት ሁኔታ እንደተፈጠረ በቁጥር 21 ላይ ጌታ ኢየሱስ ተናገረ። ይህም በማቴ 12፡6 እንደምንመለከተው ክርስቶስ ኢየሱስ ከመቅደሱ እንደሚበልጥ ስለዚህም ከመቅደሱ ይልቅ እግዚአብሔር በሰዎች መካከል መገኘትን በክርስቶስ ኢየሱስ እንደሚፈፅም ያሳየናል። እርሱም በገባው የተስፋ ቃል መሠረት /ማቴ 18፡20/ ሁለትም ሶስትም ሆነን በስሙ በተሰበሰብንበት በመካከላችን ስለሚገኝና ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ የአዲስ ኪዳን ክርስቲያን አማኝ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ /ማደሪያ/ ስለሆነ /1ኛ ቆሮ 16-17/ 2ኛ ቆሮ 6፡16-18 , ኤፌ 2፡19-22, 1ጴጥ 1፡4-5 አማኞች በክርስቶስ ኢየሱስ ስም

በተሰበሰቡበት ስፍራ ሁሉ እግዚአብሔርን ማምለክ እንደሚችሉ እንመለከታለን።

2) በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ እንዲሁም ዕርገት ጋር በተያያዘ ከተከፈተው አዲስ የደህንነት መንገድና በተሰጠውም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ /ዮሐ 7፥37-39/ የተነሳ ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋ ሁሉ ከዘርም ሁሉ እውነተኛ አምላኪዎችን እንደዋጀ ልንረዳው በምንችለው ሁኔታ ዮሐ 4፥23 ላይ እግዚአብሔር የሚፈልጋቸው እውነተኛ አምላኪዎች እንዳሉ ይናገራል። ይህም አባባል የብሉይ ኪዳኑ የአምልኮ ስርዓት ከዚህ በኋላ ምንም ሥፍራ እንደማይኖረው ነገር ግን በዕብራዊያን 10፥1 እንደምንመለከተው የእውነተኛ ነገር ጥላ ብቻ እንደሆነ ያስገነዝበናል። ከቃሉም እንደምንመለከተው እነዚህ በእውነት እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ደግም ልደት ያገኙ ሲሆኑ ዮሐ 3፥18 እግዚአብሔርም እነዚህን የሚያገኛቸው በመንፈሱ ነው ማለት ነው። ይህ መንፈስ በክርስቶስ ኢየሱስ በማዳኑ ሥራ የተሰጠ እንደሆነም እናያለን።

3) ከላይ ከተገለጠው ሃሳብ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የአዲስ ኪዳንን አምልኮ ለየት የሚያደርገው ሌላው ነጥብ አምልኮው እንደብሉይ ኪዳን በውጫዊ ስርዓቶች ላይ ያተኮረ ሳይሆን ከአማኝ ውስጣዊ ህይወት በሚመነጭ አምልኮ ላይ ነው። ስለሆነም በዮሐ 4፥24 እግዚአብሔር የሚመለከው በመንፈስና በእውነት እንደሆነ ጌታ ተናገረ። በመንፈስ ሲልም በዮሐ 7፥37-39. እንደተገለፀው በክርስቶስ የማዳን ሥራ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ተቀብለው ከእርሱ ባገኙት በውስጣቸው በሚመነጨው ህያውና የተቀደሰ መንፈስ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆኑትን ነው። ይህም ማለት ከመንፈስ ቅዱስ አዲስ ልደትን የሚሰጥ የልጅነት መንፈስ ማለት ነው። በእውነት ሲልም / በዮሐ 14፥6/

እንደምንመለከተው እውነት ክርስቶስ እንደመሆኑና ለሰዎችም የእግዚአብሔርን እውነተኛ ፈቃድ የሚገልጥ እርሱ በመሆኑ፤ / ዮሐ 8፥45፤ 18፥37/ እርሱ ብቻ ሰውን ወደ አብ እውነተኛና ትክክለኛ እውቀት ስለሚያመጣ (ዮሐ 17፥3) ሰዎች እግዚአብሔርን በእምነታቸውና በመታዘዛቸው እንዲያከብሩ ያስችላል፡፡

ስለዚህ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለውና የተወደደ አምልኮ ማቅረብ የምንችለው በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በማዳኑና በማንፃቱ ስንቀርብ ብቻ ነው፡፡ (ዕብ 9፥14) በዚህም ሰዎች ምንም ያህል ቢደክሙ ዋጋ ቢከፍሉና በተለያየ መንገድም ቢተጉ ከደህንነት በፊት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው አምልኮ ማቅረብ እንደማይችሉና ትጋታቸው ሁሉ እንዲሁ ባዶ ስርዓትና ድካም እንደሆነ እንረዳለን፡፡

## 4.2. በአዲስ ኪዳን የአምልኮ መገለጫዎች

- ስብከትና ትምህርት ፡- 2ተኛ ጢሞ 4፥2

  ቃሉን ስበክ በጊዜውም አለጊዜዉም ጽና ፈጽመህ እየታገስህና እያስተማርህ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም፡፡

- የጌታ እራት፡- 1ቆሮ 11፥23-26, ማቴ 28፥19

  "እናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ አመሠገነ ቆርሶም እንካችሁ ብሉ ይህ ስለእናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፡፡ እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንስቶ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት

አለ ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና፡፡

- ✧ ፀሎት፡- ዮሐ 18, 1ጢሞ 2፡1-2

እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር ልመናና ፀሎት ምልጃም ስለሰዎች ሁሉ ስለነገስታትና ስለመኳንንትም ሁሉ እንዲደረግ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ፡፡

- ✧ ቃሉን ማንበብና ማጥናት፡- 1ጢሞ 4፡13

እስክመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ፡፡

- ✧ ዝማሬና ሙዚቃ፡- ቆላ 3፡16, ዕብ 13፡5, 1ተሰ 5፡16-18

የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ በጥበብ ሁሉ እርስ በእርሳችሁ አስተምሩና ገስፁ፡፡ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ በፀጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፡፡

- ✧ እርዳታ መስጠት፡- ዕብ 13፡6, ፊል 4፡18 ያዕ 1፡27

ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ እንዲህ ያለው መስዋዕት እግዘዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና፡፡ ንፁህ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ በዓለምም ከሚገኙ እድፍ ሰውነትን መጠበቅ ነው፡፡

## 4.2. የአዲስ ኪዳን አምልኮ መገለጫዎችን ሰብሰብ አድርገን እንደሚከተለው

ማስቀመጥ እንችላለን፡-

- ✪ ለእግዚአብሔር መናገር፡- / Talking to God/

✧ የአንድ አካል ብልት በመሆናችን እግዚአብሔርን በዜማ መሳሪያና በዝማሬ እያደነቅን እናመሰግናለን በሕብረት ፀሎት ተግተን እናደነቀዋለን እንለምነውማለን ለሚያስፈልጋቸውም በመለገስ /ወላጆች የሌላቸውን ልጆችና ባልቴቶችን፡- ያዕ 1፡27) ንፁህ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ እናቀርባለን፡፡

✪ እግዚአብሔርን መስማት፡- /Hearing God/

✧ እግዚአብሔር በልዩ ልዩ መልኩ ሲናገረን መስማትና መተርጎም አስፈላጊ ነው፡፡ እርሱ ሲያነሳሳንና ማንቱን በየዕለቱ ሲገልጽልን ትክክለኛውን አምልኮ ለማቅረብ ኃይል ይሆንልናል፡፡ የኃይሉን ታላቅነት በይበልጥ ስንረዳ ፍቅሩንና ባህሪውን ስናስተውል ክብር የሚገባው መሆኑን ተገንዘበን በመንፈስና በእውነት ማምለክ እንጀምራለን፡፡ (ኢሳ 6፡1-8)

✪ ምላሽ መስጠት፡- / Give Response/

✧ ስለእግዚአብሔር ማንነት ስላደረገልንና ስለሚያደርግልን ነገር ባወቅንና በተገነዘብን ቁጥር በተግባር ምላሽ ልንሰጥ የሚገባውን እግዚአብሔርን ማምለካችን ነው፡፡ (ኢሳ 6፡1-8/

✧ እንግዲህ ልባችን በቃልና በዜማ ራሱን ሲገልጽ አእምሮአችን እግዚአብሔር የሚፈልገውን ለመለየትና እንደፈቃዱ ለማድረግ ሲመረምር አካላችንም በተግባር ራሱን አዘጋጅቶ ሲገኝ እግዚአብሔርን እያመለክን ነው፡፡

✪ እውነተኛ ስሜት / Truth Feeling /

✧ አምልኮ በእግዚአብሔር ደስ የመሰኘት ነገርም ስለሆነ ስሜቶቻችንንም ይጨምራል፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር ግብዝነትን ስለሚጠላ በጥልቅ ስሜት ልናመልከው ይገባል እንጂ በማስመሰል ስሜት መሆን የለበትም፡፡ ስለዚህ አምልኮ ትክክልም እውነተኛው መሆን አለበት፡፡

- ✧ እውነተኛ ስሜት ደስታን እንደሚያስከትል የሐዋ ሥራ 2፡42-46 እንደዚህ ይገልጸዋል፡፡ “ በሐዋሪያትም ትምህርትና በህብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየፀሎቱም ይተጉ ነበር፡፡ በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ፣ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፡፡

✪ *መደምደሚያ፡-*

- ✧ የአዲስ ኪዳን አምልኮ መገለጫዎችን ሰብሰብ አድርገን ስናይ ለእግዚአብሔር መናገር፣ እግዚአብሔርን መስማት፣ ምላሽ መስጠትና እውነተኛ ስሜትን በመግለጽ ላይ ያተኮሩ ናቸው ማለት እንችላለን፡፡ እግዚአብሔርን መለመንና በልዩ ልዩ መልኩ ሲናገረን መስማትና በተግባር መተርጎም ስለ እግዚአብሔር ማንነት ስላደረገልንና ስለሚያደርግን ነገር፤ ባወቅንና በተገነዘብን ቁጥር በተግባር ምላሽ መስጠትና በመንፈሳዊ ስሜት በፊቱ መደሰት የዘወትር ተግባራችን ሊሆን ይገባል፡፡ ስለዚህ ሰዉ በህብረት ስያመልክ የጌታን ፀጋ ባንድነት ይካፈላል! ! የመፈጠራችን በምድር ላይ የመኖራችን ዋነኛ ምክንያት እግዚአብሔርን ለማምለክ ነዉ፡፡ <<የአዲስ ክዳን አምልኮ ማዕከል ክርስቶስ ነዉ፡፡ >>

# ምዕራፍ አምስት

*“ታምራት የማይሠራበት ጊዜ ባይኖርም አምልኮ ላይ ግን ልዩ ኃይል ይገለጣልና ልዩ ታምራት ታያለህ፡፡”*

## 5. እውነተኛ አምልኮ /Truth worship/

*ዓላማው፡- እግዚአብሔር እውነተኛ አምልኮዎችን ስለሚፈልግ እርሱን በማወቅ ከልማዳዊ አምልኮ ባለፈ መልኩ በመንፈስና በእውነት ማምለክን እንድንለማመድ ነው፡፡*

ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ የሚቻለው በክርስቶስ ኢየሱስ አማካኝነት ብቻ ሲሆን ከልብ የሆነ አምልኳችንም የሚከናወነው በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት ብቻ ነው፡፡ ይህንን ስንል መንፈስ ቅዱስ አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ “በልባችን ይልካል (ገላ 4፥6) ያም መንፈስ የእግዚአብሔር ልጆ መሆናችንን ይመስክራል፡፡ (ሮሜ 8) ይህ የመንፈስ አንድነትም ነው እግዚአብሔርን እንደ ፈቃዱ እንድናመልከው የሚያስችለን፡፡ በማይሰማ መቃተትም ይፀልይልናል / ሮሜ 8፥26) ይህም ማለት ጌታ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሆኖ ጌታ ኢየሱስን ከፍ ከፍ እንድናደርገውና እንድናመልከው ያደርገናል፡፡

ስለዚህ የአምልኮ ትኩረት ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ላይና ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሆነ እንቅስቃሴ የአመላለክ ሁኔታ ላይ ያተኮረና ሕይወት የለሽ ስርዓት ብቻ ነው፡፡

## 5.1. ልዩ ልዩ አምልኮ፡-

ጌታ ኢየሱስ ለሳምራዊቷ ሴት ስለ ሦስት ዓይነት አምልኮ ሲያብራራ እንመለከታለን፡፡ ይኸውም

1) “እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ (ዮሐ4፡22) ማለት ያለ እውቀት ስለሆነው የሳምራውያን አምልኮ
2) “እኛ መዳን በአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን" (ዮሐ 4፡22) በማለት በዕውቀት ስለሆነውና አዳኙን ስላላስተዋለው የአይሁዳውያን አምልኮ
3) “ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፡፡ አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ያሻልና፤ ዮሐ 4፡23) በማለት ስለእውነተኛው አምልኮ ይነገራል፡፡

ሳምራውያን አምስቱን የሙሴ መጽሐፍ በመጠቀም ስለ እግዚአብሔር ጥቂት እውቀት እንደነበራቸው የስነ መለኮት ሰዎች ይናገራሉ፡፡ በአንፃሩ አይሁዳውያን ደግሞ በብሉይ ኪዳን መሰረት ብቁ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት እንደነበራቸው ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ግን በእውነትና በመንፈስ አልነበረም፡፡ በዚህ ዘመንም ያው የአምልኮ አይነት ከዚህ አመዳደብ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

*“ነገር ግን በእውነት የሚሰግድ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደእነዚህ ያሉን ያሻልና፤ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል፡፡” (ዮሐ 4፡23-24)*

## 5.2. ስፍራ የማይገታው አምልኮ፡-

ከሳምራዊቷ ሴት ጌታ ኢየሱስ ስፍራ የማይገታው አምልኮ እንደመጣና ወቅቱም በዚያኑ ዕለት እንደነበር ገለጸላት፡፡ ጌታ ኢየሱስ ይህንን ማለቱ አምላካችንን በቦታ በአካባቢና በውጫዊ ነገሮች ሳንለካና

ሳንገድብ በጊዜውም አለጊዜውም ውስጣችን በፈሰሰው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ማምለክ እንደምንችል ማሳየቱ ነው። (ዮሐ 4፥21)

## 5.3. በመንፈስና በእውነት ማምለክ፡- ዮሐ 4

ከይሁዳ ወደ ገሊላ ሲሄድ የተራራውን ሸንተረር ከጨረሰ በኋላ ኢየሱስ በሰማሪያ በኩል የግድ ማለፍ ነበረበት። እርሱም "ሲከር" በምትባለው ቦታ ባለችው የውሃ ጎድጓድ አጠገብ ተቀምጦ ለመነጋገር በእርግጥም ቦታው አይመስልም። እንዴት የሰማሪያ ሴት ውሃ ልትቀዳ ወደጉድጓድ መጣች። ማንም ሰው ቢሆን ከእርሷ ጋር ለመነጋገር የሚመርጣት ሴት አልነበረችም። ለነገሩ ሴትየዋ ብዙም ለመወያየት የምትፈለግ አትመስልም። ንግግሩን ባጭሩ ብትቋጨው ደስ የምትሰኝ ትመስላለች። እርሷ ውሃ ልትቀዳ ስትመጣ የማታውቀው ሰው ተቀምጦ ታያለች የደከመውና የሚያሳዝን ሰው ነው። የተጠማ ይመስላል ታዲያ አይሁዳዊ ቢሆን ኖሮ አንኳን ሊያነጋግራት ቀርቶ እርሷ ባለፈችበት እንደማያልፍ ታውቃለች። ለእርሷና ለዘሮቿ አይሁዶች የመጨረሻ ጠላቶቹዋ ናቸው።

አይሁዶች ከማንም ይልቅ ጥሩ የሆነ ነገር እንዳላቸው ያስባሉ እግዚአብሔር የወደደው እነርሱን ነው። ንፁህ ስም አለን ብለው ስሚያስቡ ከማንም ዘር ጋር እንዲቀላቀልባቸው አይፈልጉም ከሁሉ በላይ እግዚአብሔር የሚገኝበት መቅደስም ያለው እነሱ ዘንድ ነው።

ስለዚህ አንድ አይሁዳዊ ምንም ያህል ቢጠማ ከሰማሪያዊት ኩባያ ውሃ አጠጭኝ አላት የሚያስደንቅ ነገር ነው። ጆሮዋ ማመን አልቻለም። ሳምራዊት መሆኔን እንዴት ማወቅ አልቻለም ወይስ አውቆ ይሆን አለች። ሰውየው ግን ደግሞ ተናገራት "ውሃ አጠጪኝ የምልሽ ማን መሆኑን ብታውቂ ራስሽ ትለምኝው ነበር የሕይወትም ውሃ ይሰጥሽ

ነበር።" አላት። "ምን ማለቱ ነው እንኳን ለእኔ ሊያመጣ እርሱ ራሱ የሚያመጠጣበት እቃ የለውም። ጉድጓድ ደግሞ ሩቅ ነው ምን እንደሚል በእርግጥ ያውቃል? ውሃ ልጠጣሽ እንዴት ይላል ደግሞ የሕይወት ውሃ ወንዝ ማለቱ ሞኝ ነው ይሆን? ከዚህ ጉድጓድ ሊሻል የሚችል ወንዝ በቅርብ የለም ለመሆኑ ስለራሱ ምን አስቦ ነው ይኼን የሚናገረው?" ብላ አለች። አሁንም ለየት ባለ አነጋገሩ መናገር ቀጠለና እንዲህ አለ። "ከዚህ ውሃ የሚጠጣ ዳግመኛ ይጠማል እኔ ከምሰጠው ውሃ ግን የሚጠጣ ለዘለዓለም አይጠማም ከሆዱ ለዘለዓለም የሚፈልቅ የሕይወት ውሃ ወንዝ ይሆናል" አለ።

ሴትየዋ ይሔ መቼም በጣም ጥሩ ነው ብላ አሰበች። ሁልጊዜ ውሃ ለመቅዳት ከመድከም ይሻላል። አለችና "እባክህ ይህንን የምትለውን ስጠኝ" አለችው። በዚህን ጊዜ እርሱ "ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ነይ" አላት። ሴትየዋም ድንግጥ ብላ " ባል የለኝም" አለች እርሱም ቀጠል አደረገና "ባል የለኝም በማለትሽ እውነት ተናገርሽ ምክንያቱም እስከአሁን አምስት ባሎች ነበሩሽና አሁን አብሮሽ የሚኖረው ደግሞ ባልሽ አይደለም ስለዚህ የተናገርሽው ትክክል ነው" አላት የሚያስገርም ነገር ነው። እንዴት አወቀ? ይህን ሰውዬ በእርግጥ ከዚህ በፊት አይቼው አላውቅም ነገር ግን ምንም ሳይቀር ታሪኬን ሚስጢሬን ሁሉ እንዴት አወቀ? እርሷ እንኳን መቁጠር የዘነጋችውን የድሮ አምስቱን ባሎቿን ሁሉ አውቋቿል። እንደዚህም ሆኖ እንኳን ሳይጸየፋት አሁንም እያነጋገራት ነው። እውነተኛ አይሁድ ቢሆን ኖሮ ከሰማሪያ በፍጥነት ይወጣ ነበር። ከማያውቁት ሴት ጋር ደግሞ አይነጋገርም ነበር። አግብቶ ፈት የሆነችን ሴት ቢያገኟት ኖሮ ይወግሯት ነበር። ይኼ ሰው ግን የተለየ ነው ምናልባትም ሰማሪያን ወደቀደመው

ቦታዋ ለመመለስ የመጣ ነብይ ኤልሳዕ ይሆናል፡፡ ደግሞ በፊገግታ እያናገራት የባሎቹዋን ስም ሳይነግራ አልቀረም፡፡ ምናልባትም የተጋቡበትን ቀንና ዓመቱንም ጭምር እና እያንዳንዱ በምን ምክንያት እንደፈረሰና እንደተበላሸ ጭምር ሳይነግራት አልቀረም፡፡

ነብዩን ከዚህ በፊት አግኝታ ወይም አነጋግራ አታውቅም ታዲያ ይኼ ሰው ከእርሷ ምንድነው የሚፈልገው? ከዚህ በፊት እንደተበላሸ የነገራትንት ሁሉ እንዴት ማስተካከል ይችላል? ምናልባት በልቧ ስለእኔ መናገር ይብቃህና እስቲ ሌላ ነገር እንነጋገር ያለች ትመስላለች፡፡ “እንደማየው አንተ ነብይ ነህ፡፡” ወደ ገሪዛን ተራራ እያመለከተችው “አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ እናንተ አይሁዶች ደግሞ ሰው መስገድ ያለበት በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ” አለችው፡፡ ገሪዛን ተራራ ኢያሱ እስራኤላዊያንን ሰብስቦ የባረካቸው ቦታ ነው፡፡ ዘዳ 27፡62 ይህ አባባሏ የሰማሪያንና የአይሁድን ውስጣዊ ቅራኔ የያዘና አርዕስቱ አምልኮን የተመለከተ ሃሳብ ነው፡፡ ለመሆኑ ምን ይመልስ ይሆን? ወገናዊነቱስ ያሳይ ይሆን? ባህላችንንና ታሪካችንን ያፈርስ ይሆን? ወይስ ያው እንደሌሎቹ አይሁዳውያን አንድ የአይሁድ መንግስት ብቻ ለመፍጠር የተነሳ ነው? የተለያዩ ሐሳቦችን ሳታስተናግድ አልቀረችም፡፡ ነገር ግን ለሴቱቱ ሲመልስ እንዲህ አላት “አንቺ ሴት እመኚኝ እግዚአብሔርን በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም የማታመልኩበት ሰዓት ይመጣል እናንተ ሳምራዊያን ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ እኛ ደግሞ ለምናውቀው እንሰግዳለን፡፡ ምክንያቱም ደህንነት ከአይሁድ ነውና፡፡ ለዚህም ሰዓት ይመጣል አሁንም መጥቷል ይህም የሚሆነው የሚያመልኩትን ሰዎች እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ ስለዚህም የሚያመልኩ በእውነትና በመንፈስ ሊያመልኩት ይገባል፡፡"

ብሎ ተናገራት። ምናልባት ይህ ለእርሷ ሳይከብዳት አልቀረም። ከበድ ያለ ትምህርት ሆኖም ግን በጣም አስፈላጊ የሆነ ሃሳብ ያዘ ንግግር ነው በተለይ “..ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኗል” ቁጥር (ዮሐ 23) የሚለው ላይ ሃሳቧ አተኮረ ። ስለዚህም “ክርስቶስ የሚባል መሲህ እንዲመጣ አውቃለሁ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል” አለችው። /ቁጥር 25/ ምናልባት በአይሁድና በሳምራውያን መካከል ያለውን ችግርና አለመግባባት ሁሉ ይፈታዋል ያስወግደዋል ማለቷም ነበር። ኢየሱስም “የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ አላት"።

ብዙ ጊዜ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ 4 ላይ የተናገረውን በተለያየ መንገድ ይረዱታል። ሊያስረዱም ሲሞክሩ እንደዚህ ይላሉ እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ የትም ቦታ ብታመልኩ ምንም አይደለም። ስለዚህ በመንፈሳችሁ መንፈስ የሆነውን አምላክ የትም ቦታ ሆናችሁ አምልኩት ይላል። ሃሳቡ ጥሩ ይመስላል ሆኖም ግን ጌታ ኢየሱስ የተናገረው ይህን አልነበረም። ለመሆኑ “እግዚአብሔር መንፈስ ነው” ማለት ምን ማለት ነው?

አዲስ ኪዳን ውስጥ “በመንፈስ ሁኑ” ብሎ ሲናገረን ለመንፈስ ቅዱስ መገዛትን ራሳችሁን አስለምዱ ማለት ነው። ይህም ማለት መንፈሳችንንና አካላችንን በአጠቃላይ ማለቱ ነው። ስለ ሥጋም ሲያወራ መንፈስ በእኛ ላይ እንዳይሰለጥን አለመፍቀድን ሲያብራራ ነው። ይህ ማለት የሥጋችንን ስሜት መከተልና በዛም መመላለስን ይገልፃል። ይህም አካል ብቻ የሆነ መንፈስ ግን የሌለው እንደማለት ነው። ለነገሩ በሁለቱም መንገድ አካል አለን። ጥያቄው ማን እየተቆጣጠረው ነው የሚለው ነው።

በግሪክና በሂብሩ ትርጉም ውስጥ መንፈስን ከእስትንፋስ ጋር አያይዞ ይገልፀዋል። ይህ ምን ማለት ነው? የማይተነፍስ አካል የሞተ

ነው፡፡ ጳውሎስ ታዲያ ስለመንፈስና ስለሥጋ የተናገረው ይሄ ነው፡፡ መንፈስ ከሌለን በድኖች ነን፡፡ ምናልባት የተለያየ ሥራ እንሰራ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን በየቀኑ እየበሰበስን ነው ማለት ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔር መንፈስ ነው ሲለን አካል የለውም ማለቱ አይደለም፡፡ እንዲህማ ከሆነ የራሱን ማንነት እየካደ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይል የነበረው እግዚአብሔር መንፈስ ነው እስትንፋስ ነው ያውም የሕይወት እስትንፋስ ነው፡፡ በሰዎች ውስጥ የሚኖር መንፈስ ነው ማለቱ ነው፡፡ በዘፍ 2፡7 እግዚአብሔር አዳምን ከምድር አፈር አዘጋጅቶ በአፍንጫው ሕይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት፡፡ በሌላ ቦታ ደግሞ "ፍጥረታችንን እርሱ ያውቃል፡፡" አፈር እንደሆንክ አስብ" መዝ 103፡14፡፡ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መንፈስ ግን ሕይወት ይሰጣል፡፡

ታዲያ ኢየሱስ ይህን ሁሉ ለሴትየዋ ለምን መናገር አስፈለገው? እግዚአብሔር መንፈስ ነው ለምን አላት? ምክንያቱም ይህች ሴት እየሞተች ነበር የውሃ መቅጃዋን ይዛ ከጉድጓድ ውሃ ለመቅዳት ስትመጣ ከምትራመድበት አቧራ የተለየ ሰው እንደሆነች አየች፡፡ ጥማቷን ልታረካ ነው የመጣችው ሆኖም ግን ዘላቂ እርካታ የሚሰጥ አይደለም የሕይወት ውሃ ያስፈልጋታልና፡፡

በአዲስ ኪዳን አነጋገር ይህች ሴት ሥጋዊ ነበረች፡፡ ፍቅርና እንክብካቤ ከመፈለግ የተነሳ ከአንዱ ወንድ ወደ ሌላው ስትዞር ኖራለች፡፡ ምናልባትም ለትዳር ያላት መሰጠት ታምኝነት ሁሉ ተሟጦ አልቋል፡፡ ስለዚህም ይመስላል አሁን አብራው ከምትኖረው ወንድ ጋር በጋብቻ አልተጣመረችም ነበር፡፡ በውስጧ የሚነፍስ የሚንቀሳቀስ የሕይወትና የደህንት መንፈስ አልነበረባትም፡፡ እስትንፋስ የሌለባት አፈር ብቻ ነበረች፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን በተለምዶ አምልኮም ከአፏም

እንኳን ቢሆን ተቆርቋሪ ነበረች በእርግጥ በገሪዛን ተራራ ላይ እየሄደች ታመልክ እንደሆን በግልጽ የምናውቀው ነገር የለም፡፡ ሆኖም ግን ስለዚህ ስለተራራው አምልኮ ለመከራከር ሽንጧን ገትራ የቆመች ትመስላለች፡፡ ኢየሱስ በገሪዛን ተራራ ላይ ስለማምለክ ሁለት ችግሮች እንዳሉበት ተመልክቷል፡፡

ስለዚህ ይህንን በግልጽ አብራራላት አንደኛው ስለመቅደስ አምልኮ ነው ኢየሱስ ሲናገር "በዚህም ተራራ ሆነ በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል" እዚህ ላይ እናስተውል ኢየሱስ ሲናገር በሁለቱም ቦታ ማምለክ መጥፎ ነው አላለም፡፡ የአምልኮ ቦታ ሄዶ ማምለክና ባህልን ተከትሎ ማምለክ ስህተት ነው አላለም፡፡ ለነገሩ የመቅደስ አምልኮ ከአይሁድ ጋር የተለያየ ነው፡፡ ነገር ግን ሙሉ የሆነ አልነበረም፡፡ ያንን ሊሞላ የህግ ፍፃሜና ሙላት ሆኖ የመጣው ደግሞ ራሱ ኢየሱስ ነበረ፡፡ ይህንንም በአገልግሎቱ መጀመሪያ በማቴ 5፡17 ላይ ገልጾታል፡፡ "እኔ ህግንና ነቢያትን ለመሻር አልመጣሁም ልፈጽም እንጂ" ብሏል፡፡

በኋላም ጳውሎስ በገላትያ 3፡24 ላይ እንደዚህ ብሎ ገልፆታል "በእምነት እንፀድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ነው" ሕግ ወደ ዋናውን ነገር የሚያደርስ እንደሆነ ገልፆታል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ጳውሎስ ሕግን እንደሥጋ አሠራር አድርጎ ይገልፀዋል፡፡ እኛም በዛ በኩል ልናይ ይገባል፡፡ ሕጉ የተሰጠው በእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ 2ጢሞ 3፡16 ቅዱሳት መጽሐፍት ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ እስትንፋስ እንደተፃፉ ይገልፃል፡፡ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ በተጻፈው ቃል ውስጥ ሲያልፍ ሕጉ የዚያን ጊዜ የሚጠቅም ይሆናል፡፡

ሕጉ የተፃፈው ወደ ክርስቶስ እንዲያደርስ ነው፡፡ ስለዚህ ሕጉ ያለመንፈስ የሚሰጥ ሥጋዊነት ብቻ ነው፡፡ በ2ኛ ቆሮ 3፡6 "ሕግ

ይገድላል መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል" ይለናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ እስካለፈ ድረስና ወደ ክርስቶስ የሚያደርስ ከሆነ ሕጉ ጥሩ ነው፡፡ ከመንፈስ የተለየ ሕግ ግን በራሱ የሞተ ነው፡፡ ለሚከተለውም ሕይወትን አይሰጥም አላት፡፡

በጌታ ኢየሱስ ቃል በኢየሩሳሌም /ቤተ-መቅደስ/ እና በሰማሪያ ተራራ ስላለው አምልኮ የተገለፀውም ይህንኑ ያብራራል፡፡ ምናልባትም ጌታ ይህንን ሲናገር ወደፊት በ70 ዓ.ም በኢየሩሌም ሊፈፀም ያለውን የቤት መቅደስ መፍረስ ተመልክቶ ይሆናል፡፡ የአምልኮ ቦታዎች ወይም ቅርጾች ለአጭር ጊዜ ጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ ግን ጊዜያዊ ናቸው፡፡ ሕጉን የሚጠብቀው ሰው የመንፈስን አሰራር ከረሳና ከተወ ሕጉ የማይጠቅም ይሆናል፡፡

ስለዚህም ነው ጌታ የሴትየዋ አምልኮ የማይጠቅም ከንቱ ልፋት እንደሆነ የነገራት፡፡ ሁለተኛው ችግር ደግሞ በሰማሪያ ያለው አምልኮ ነው፡፡ ይህ አምልኮ በእውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ላይ የመሰረተ አልነበረም፡፡ "እናንተ ሳምራውያን ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ እኛ ግን ለምናውቀው እንሰግዳለን ደህንነት ከአይሁድ ነውና፡፡ "አላት፡፡ ጳውሎስም በአቴና በሚዘዋወሩበት ጊዜ "ለማይታወቅ አምላክ " የሚል ቃል መናገሩ እነዚህ ሰዎች አምላክ መስሎ የሚታያቸው ነገር ሁሉ ጣዖት ነበር፡፡

ስለዚህ ጳውሎስ ይህን የማያውቁትን ማን እንደሆነ ልንገራችሁ ብሎ ስለፈጠረ ስለጌታ ኢየሱስና ኢየሱስን ከሞት ስላስነሳው ስለእግዚአብሔር ነገራቸው፡፡ (ሐዋ 17) ዛሬም ቢሆን ብዙ ሰዎች የማያውቁትን ያመልካሉ፡፡ እርዳታ የምንፈልግበት ጊዜ ይመጣል፡፡ አንድ ቦታ አለ እያሉ ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን በጥልቀት ስለዚህ ስለሚያመልኩት ለማወቅ አይፈልጉም፡፡ ብዙ ሀይማኖቶችም ስለሀይማኖታቸውም ብዙ

ምስክር የሆነ ነገር አላቸው፡፡ እኛ ማወቅም አንችልም ለማወቅም አልተፈቀደልንም ይላሉ፡፡ እርግጥ ነው ስለ እግዚአብሔር ሁሉንም አናውቅም፡፡ ብዙ የማናውቀው ነገር አለ፡፡ ሆኖም ግን እግዚአብሔር ማወቅ የሚገባንን ሁሉ ገልጾልናል፡፡ ከዚህም የተነሳ ነው የኢየሩሌምና የሰማሪያ ስግደቶች የተለያዩት ሁለቱም ግን መንፈስ የሌላቸው አምልኮዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን አይሁድ /የኢየሩሳሌም/ አምልኮ በትክክል ቢገለገሉበት ወደ ክርስቶስ ሊያደርሳቸው የሚችል ነበር፡፡

የተፃፈው መጽሐፍ፣ የተሰራው ቤተመቅደስ፣ እና የተተነበየው ትንቢት ሁሉ ቢመረምሩት ስለእግዚአብሔር የተነገረ ከእግዚአብሔርም የተሰጠ ነው፡፡ ወደ ክርስቶስም የሚያደርሰንን እውነት የያዘ ነው፡፡ ሰማሪያውያን ግን ያልታዘዙ ተራራ ላይ ይሰግዱ ነበር፡፡ መዳን ከአይሁድ ነው የሚለው አባባል በተለይ ሰማሪያውያን ሊሰሙት የማይፈልጉት ንግግር ነው፡፡ የበላይነትን የሚያንጸባርቅ ይመስላልና፡፡ ኢየሱስ እዚህ ላይ ከባህርዊ ስሜት የተነሳ የሚናገረው ንግግር አልነበረም፡፡ በእርግጥ እርሱ አይሁድ ነው፡፡ ምንም እንኳን አሁን በሰማሪያ በኩል ቢጓዝም አብዛኛው የምድር ሕይወቱን ያሳለፈው በገሊላ ነው፡፡ ያደገው እዛው ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አሁን የሕግ ፍፃሜ ሙላት ሆኖ ከዚያው ከአይሁድ ከፍል መጥቷል፡፡ አዎ እርሱ ራሱ የሚጠበቀው መድሃኒትና አዳኝ ነው፡፡

ለሴትየዋ ይህንን መስማት አስቸጋሪ ሳይሆንባት አይቀርም ምናልባት ስትማር የቆየችው በገሪዛን ተራራ ማምልክ በኢየሩሳሌም መቅደስ ከማምለክ ጋር እኩል ነው የሚል ይሆናል፡፡ ያንን ሀሳብ ስታቀርብ ኢየሱስ የሚስማማ መስሏት ነበር፡፡ የኢየሱስ መልስ ግን አዎን አይደለም ነበር፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ከሌለበት ሁለቱም ልዩነት የላቸውም፡፡ ሁለቱም የሞቱ ናቸው አላት ነገር ግን የሰማሪያዊያን

እምነት ሳይሆን የአይነሁድ እምነት  እውነት ወደሆነው ወደ ክርስቶስ ሊያደርስ እንደሚችል በውል አስረዳ፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ አስተያየቱን ሁሉ በሁለት ቃላት ደመደመ “ መንፈስና እውነት በሚባሉ ቃላት፡፡ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ እውነተኛ አምልኪዎች በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል” ሲል ተናገረ፡፡

ስለ እንዚህም እውነተኛ አምላኪዎች ሲናገር በመጀመሪያ ስለጊዜ ተናገረ “ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኗል” ብሎ ሲናገር ምንድ ነው ልዩነቱ? አሁን ሆኗል ብሎ ሲናገር እንዴት ሊያውቅ ቻለ? ምን ማለቱ ነው? የእርሱ በዚህ ቦታ መገኘት መልሱ ነው፡፡ ዓለም ለዘመናት ሲጠብቀው የኖረው እርሱ ነው፡፡ ሥጋ የሆነው መንፈስ፣ ቃል የሆነው ስጋ እርሱ ነው፡፡ እርሱ ደግሞ እውነት ነው፡፡ እርሱ ሰዎች እግዚአብሔርን በእውነት እንዲያመልኩት ያደርጋል፡፡ በመንፈስና በእውነት ማምለክ ምን ማለት ነው? በመንፈስ ማምለክ ማለት መንፈስ በውስጣችን እንዲሰራ መፍቀድ ነው፡፡

ሰውነታችንን አልፎ አእምሮአችንን በማነቃቃት ማንን እንምናመልክና ለምን እንደምናመልክ ይረዳናል፡፡ እንደዚሁም ሰውነታችን (አካላችን) እግዚአብርን በሚያስደስት መልኩ እንድናመልክ ኃይላችንን ያድሳል፡፡ በብዙ መንገድ መንፈስ ቅዱስ ራሱን ለእኛ ይገልፃል፡፡ በሕይወታችን እንዳየነው ሁሉ እርሱ ሕይወት መንፈስ ነው፡፡ እርሱ የኃይል መንፈስ ነው፡፡ የእርሱን ስራ በአምልኮአዊ ስርዓቶች ልንገልፀውም አንችልም፡፡ በየቀኑ ኑሮአችን ውስጥ በመግባት ይመራናል፡፡ ከሁሉም በላይ እርሱ የክርስቶስ መንፈስ ነው፡፡ የእግዚአብሔር የመገለጡ ሙላት የታየበት የክርስቶስ መንፈስ ነው፡፡

ኢየሱስ ስለእውነት ሲናገር ስለራሱ መናገሩ ነበር፡፡ "እኔ እውነት ሕይወት መንገድም ነኝ" አለ፡፡ ዩሐ 14፥6 በሌላ ቦታ ደግሞ "እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያጣችኋል" አለ፡፡ ዮሐ 8፥32 በዚህ ቦታ ኢየሱስ ስለ እኔ የተነገረውን እውነት ታውቃላችሁ፡፡ የእኔን እውነት ታውቃላችሁ፡፡ በእውነትም እኔን ታውቃላችሁ አለ፡፡ ከጌታ ጋር ስንኖር እውነትን የምናውቀው በቃል ወይም ሲነገር በመስማት ሳይሆን እኛ ራሳችን በውስጡ እየኖርን ተካፋይ በመሆን ነው፡፡

ስለዚህ ኢየሱስ በእውነትና በመንፈስ እግዚአብሔርን አምልኩ ብሎ ሲናገር ልናስታውሰው የሚገባን ነገር በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተገለጠው የእግዚአብሔር እውነት ሁሉ ወደ እርሱ እንደሚመራን ነው፡፡ እርሱ ደግሞ እግዚአብሔርን ለማምለክ መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ሁሉ በኢየሱስ ውስጥ መምጣት አለባቸው፡፡

ያለ እኔ ማንም ወደ አብ ሊመጣ አይችልም (ዮሐ 14፥6) በኢየሱስ ውስጥ ሆነን ልናመልክ ያስፈልገናል፡፡ ይህንን ሲል በክርስቶስ እውነት ውስጥ መገኘት ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በመጀመሪያ በክርስቶስ ውስጥ መገኘት አለብን፡፡ በግላችን ልናውቀውና በመንፈስ ዳግመኛ የተወለድን መሆን አለብን፡፡ ይህ በእውነት እንድናመልከው ቀዳሚ ሁኔታ ነው፡፡ በአምላካችን ውስጥ የጌታን እውነት መናገርና መግለጽ ትልቅ ቦታ አለው፡፡

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ ሰዎች በአምልኮ ጊዜ ደግመው ደጋግመው ጮክ ብለው የእግዚአብሔርን እውነት በመናገርና በመደጋገም ያሰሙ ነበር፡፡ "አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" "ይገባሃል የዓለምን ሀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" የሚሉትና የመሳሰሉት ሀሳቦች ይህን እውነት ይገልጽ ነበር፡፡ በዮሐ 4 በሳምራዊቷ

ሴት ጋር በተደረገው ንግግር መጨረሻ አብሯት የነበሩትም የመንደሩ ነዋሪችም “ እርሱ የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ ነው” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እኛም ብዙ የምናስተጋባው እውነት አለን፡፡ በሌላ መንገድም ይህ የሚያሳየን አምልኳችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተገለፀው እውነት ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆን እንደሚገባው ነው፡፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ መጽሐፍ ቅዱስና ጌታ ኢየሱስ አንድ እንደሆኑ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ቃሉ ስለ ኢየሱስ ይመሰክራልና እንዲያውም ኢየሱስ አንዳንዴ “ቃል” አንዳንዴ ደግሞ “እውነት” እየተባለ በዚህ ክፍል ቃል ውስጥ ተገልጿል፡፡

በእውነት ማምለክ ማለት በክርስቶስ ማምለክ ማለት ነው ይህም መንፈስ የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም ለክርስቶስ ይነግርልናል ለእኛም ያሳውቀናል ማለት ነው፡፡

እንግዲህ እግዚአብሔርን በሞተ የሕግ ሥርዓት ማምለክ ሳይሆን በሚያንፀባርቅና ሕያው በሆነ በመንፈስና በእውነት እናምልከው፡፡ ዛሬም ቢሆን በእውነተኛው ነገር ላይ የሚነሱትን ሁሉ መዋጋት አለብን፡፡ አንዳንዶች ህጋዊነት ሕይወት ከውስጡ በማስወጣት ሕግን ብቻ ይሰብካሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ እውነተኛ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያልተመሰረተ የተለያየ ሃሳብና ስሜት ያንፃባርቃሉ፡፡

እኛ ግን በእውነትና በመንፈስ አምላካችንን ልናመልከው እንነሳ ! !

*መደምደሚያ፡-*

እውነተኛ አምልኮ እግዚአብሔር ደስ በሚለው መልኩ እናምልከው ዘንድ በመንፈሱ የሚገለጽልንና የምንተገብረው መንፈሳዊ እውነት ነው፡፡ ስለዚህ አምልኮአችን ክርስቶስ ማዕከል ያደረገ ይሁን፡፡

**“ዘመኑ ቀርቧልና የሚያነበው የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተደረገውን የሚጠብቁት ብፁአን ናቸው”።** (ራዕ 1፥3, ማቴ 8ለ17-19)

## ዋቢ መጽሐፍ / Bibliography/


- ✧ መዝገበ አምልኮ (በአማርኛ) ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ 1992 ዓ.ም
- ✧ መጽሐፍ ቅዱስ (በግዕዝና በአማርኛ) ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1984 ዓ.ም
- ✧ መዝሙረ ዳዊት (ንባብና ትርጉሜው) ተስፋ ገ/ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1982 ዓ.ም
- ✧ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ንግድ ማተሚያ ቤት 1972 ዓ.ም
- ✧ ወንጌል ቅዱስ (ንባብና ትርጓሜው). ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት 1959 ዓ.ም
- ✧ አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ግሎብ ስነጽሁፍ አገልግሎት አ/አ 2003 ዓ.ም
- ✧ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱ የ1962 ትርጉም እና የ1993 ዓ.ም አዲሱ መደበኛ ትርጉም



ዮናስ ዘርጸ ትውልድ እና እድገቱ በምዕራብ አባያ ወረዳ ሲሆን ከልጅነቱ ጀምሮ እግዚአብሔርን በመፍራት እና በማገልገል አድጓል።
በአሁኑ ሰዓትም ጌታን እያገለገለ እና በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን እየተከታተለ ይገኛል።

"ፕሮስኩኔኦ" የግሪክ ቃል ሲሆን የተመሰረተውም በሁለት ቃል ነው። "ፕሮስ" እና "ኩኔኦ" ናቸው።ይህ ማለት "to come near and kiss" ማለት ነው ።ይህ ማለት "when there is kissing there is touching" ሲሆን "kissing" ባለበት መነካካት አለ ስለዚህ "ፕሮስኩኔኦ" ማለት "to come near and kiss" ማለት ነው። የኛ መንፈስ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ሲነካካ ወይም የእኛ መንፈስ የእግዚአብሔርን መንፈስ ሲነካ ወይም የእኛ መንፈስ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ሲዋሃድ ያ ንኪኪ ሲኖር ነው የአምልኮ ደረጃ ደረስን የምንለው።

መፅሀፉን አንብባቹ ትባረኩበት ዘንድ እየጋበዝኩ ማንኛውም አይነት አስተያየት ለመቀበል እና ለማረም ዝግጁ መሆኔን እገልፃለው።

ተባረኩ !

ዋጋው 50 ብር ብቻ

ኤደ ማተሚያ ቤት - ሀዋሳ
0930506959